
# ዓምድ 5፡- ባለአደራነት




ባለአደራነት የተቀበሉትን ለተባለው ዓላማ በአግባቡ ማዋል ነው፡፡ መጽሐፍ «ያልተቀበልኸው ምን አለ?» (፲ቆሮ 4፡7) እንደሚል መሪ «አለኝ» የሚለው መልካም ነገር ካለ ሁሉም ከእግዚአብሔር የተሰጠው የእግዚአብሔርን መልካም አምላክነት መግለጫ ነው፡፡ ስለዚህ የተቀበለውን ሁሉ በአግባቡ ማስተናገድ ወይም ማስተዳደር አለበት፡፡ ይህ መልካም ባለአደራነት[26] ነው፡፡

[26] Stewardship:- the conducting, supervising, or managing of something; especially: the careful and responsible management of something entrusted to one's care . Merriam Webster's 11th Collegiate Dictionary.





ለክርስቲያን የመጀመሪያው አደራ ለራስ ሕይወት መጠንቀቅ ነው፡፡ ይህም እያንዳንዱ ሰው እግዚአብሔርን በመፍራትና በቅድስና መኖር ነው፡፡ ሎጥ እጅግ አመፅና ኃጢአት በበዛበት ዘመን ሲኖር ራሱን በጽድቅ እንደ ጠበቀ ሁሉ (2ጴጥ 2፡8) ለግል ሕይወት መጠንቀቅ የመጀመሪያው አደራን የመወጣት እርምጃ ነው፡፡

ለክርስቲያናዊ መሪ ሁለተኛው አደራ የተሰጠውን አገልግሎት በትጋት መፈጸም ነው፡፡ ጳውሎስ እንዲያደራጅና ሽማግሌዎችን እንዲሾም በቀርጤስ ለተወው ቲቶ ለመሪነት ስለሚሾሙት ሰዎች መመዘኛ ሲጽፍለት አንዱ «እንደ እግዚአብሔር መጋቢ»[27] (ቲቶ ፲፡7) የሚል ነው፡፡ ይህም «ከእግዚአብሔር አደራን እንደ ተቀበለ አገልጋይ» ማለት ነው፡፡

በመሪነት ላይ ለሚቀመጥ ሰው በአደራ የሚሰጠው ነገር ብዙ ነው፡፡ የሚመራቸው ሰዎች፤ የድርጅቱ ተልእኮና ተግባር፤ ሥልጣን፤ ገንዘብ፤ ንብረት፤ ጊዜ፤ ሁሉ በአደራ ተሰጥቶታል፡፡ ክርስቲያናዊ መሪ የሚሾመው የእግዚአብሔር በሆነው ላይ ነውና፡፡

የአገልግሎት ራእይ ከእግዚአብሔር የተቀበለ ሰው ለተቀበለው ነገር ባለአደራ ነው፡፡ ራእዩ የሰጪው እንጂ የግሉ አለመሆኑን በመገንዘብ በጥንቃቄና ለእግዚአብሔር ክብር በመስጠት ማከናወን አለበት፡፡ ልዩ ልዩ የጸጋ ስጦታ የተቀበሉ ሰዎችም ስጦታውን ከእግዚአብሐየር በነጻ እንደ ተቀበሉ በመረዳትና በነጻ በመስጠት (ማቴ 10፡8፤ ፲ጴጥ 4፡10) መጋቢነታቸውን መፈጸም ይጠበቅባቸዋል፡፡

[27] በአዲሱ መደበኛ ትርጉም መጽሐፍ ቅዱስ - «የእግዚአብሔር ሥራ ባለ ዐደራ» ይላል፡፡ «an overseer is entrusted with God's work», (NIV). «as the steward of God;» KJV.

የክርስቲያናዊ መሪ ባለአደራነትን በተመለከተ በተለይ በሁለት ነጥቦች ላይ ትኩረት እናደርጋለን::

## 5.1 የእግዚአብሔር ሕዝብ

ለክርስቲያናዊ መሪዎች እግዚአብሔር የሚሰጣቸው ትልቁ አደራ ሕዝቡን ነው:: መሪዎች የእግዚአብሔርን ሕዝብ የራሳቸው ንብረት እንደሆነ ሳይቆጥሩ ሊመግቡት፣ ሊያሰማሩት ይገባል:: ሐዋርያው ጳውሎስ የኤፌሶንን ሽማግሌዎች ሲመክራቸው «የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቁአት ዘንድ» (ሐዋ 20:28) በማለት ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር መሆኗን ያስገነዘባቸዋል:: እነርሱ ባለአደራዎች ናቸው::

ጌታ ኢየሱስ ወደ አባቱ ከመሄዱ በፊት ለጴጥሮስ አደራ ሲሰጠው የተናገረውን ከዮሐንስ ወንጌል እንደሚከተለው እናነባለን::

«ምሳ ከበሉ በኋላም ኢየሱስ ስምዖን ጴጥሮስን:- የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፣ ከእነዚህ ይልቅ ትወደኛለህን? አለው:: አዎን ጌታ ሆይ፣ እንድወድህ አንተ ታውቃለህ አለው:: ግልገሎቼን አሰማራ አለው:: ደግሞ ሁለተኛ:- የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፣ ትወደኛለህን? አለው:: አዎን ጌታ ሆይ፣ እንድወድህ አንተ ታውቃለህ አለው:: ጠቦቶቼን ጠብቅ አለው:: ሦስተኛ ጊዜ:- የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፣ ትወደኛለህን? አለው:: ሦስተኛ:- ትወደኛለህን? ስላለው ጴጥሮስ አዘነና:- ጌታ ሆይ፣ አንተ ሁሉን ታውቃለህ፣ እንድወድህ አንተ ታውቃለህ አለው:: ኢየሱስም:- በጎቼን አሰማራ (ዮሐ 21:15-17):: አለው::

ከዚህ ክፍል ስለ መንፈሳዊ መሪነት ብዙ አንኳር የሆኑ ነጥቦችን እናገኛለን:: ከእነዚህ ውስጥ ስለ መውደድና ባለቤትነት የተነገሩት ጎልተው ይወጣሉ:: በመውደድ ስለ ማገልገል የሚለውን ነጥብ





በክፍል ሦስት በሰፋት ስለምንመለከተው እዚህ ላይ ስለ ባለቤትነት እናያለን::

ጌታ ኢየሱስ ለጴጥሮስ የሰጠው አገልግሎትን እንጂ ባለቤትነትን አይደለም:: ጴጥሮስም ከጌታ በአደራ የተቀበለው የማሰማራትና የመጠበቅ አገልግሎትን እንጂ በጎቹን የራሱ እንዲያደርጋቸው አይደለም፤ የባለቤትነት ለውጥ ወይም ሽግግር አልተደረገም:: ይህን የበለጠ ለመገንዘብ የሚቀጥለው አቀራረብ ያግዛል::

| | |
|---|---|
| ግልገሎ [ቼ] ን | ግልገሎ [ኤ] ን |
| ጠቦቶ [ቼ] ን | ጠቦቶ [ኤ] ን |
| በጎ [ቼ] ን | በጎ [ኤ] ን |

«ቼ» የሚለው ፊደል ወይም በሰዋሰው ሕግ አገናዛቢ አጸፋ የሆነው «ኤ» የሚያመለክተው ባለቤትነትን ነው:: ግልገሎች፣ ጠቦቶች፣ በጎች ሁልጊዜም የኢየሱስ ክርስቶስ ናቸው:: እርሱ በገዛ ደሙ ገዝቷቸዋል (ሐዋ 20:28):: እነዚህን «የእኔ» ብሎ ሊጠራ ጴጥሮስም እንኳን አልተፈቀደለትም:: ጴጥሮስ ባለአደራ ነው እንጂ ባለቤት አይደለም::

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በሉቃ 12:42-48 ስለ ባለአደራነት (መጋቢነት) ከሰጠው ምሳሌ የምናስተውለው የመጋቢው ተግባር በኃላፊነት የተሰጠውን በመልካም እንዲያስተዳድርና ለእያንዳንዱም የሚገባውን እንዲሰጥ ነው:: ባለአደራ ሰው አደራን የተቀበለ ስለሆነ የተሰጠውን በታዘዘው መሠረት ፈጽሞ ማወራረድ አለበት:: ስለዚህ ከባለአደራነት ጋር ተጠያቂነት አብሮት አለ::

አገልጋዮች ስለ ሥራቸው በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት እንደሚቀርቡ አውቀው (2ቆሮ 5:10) ለሚያገለግሉትም ምእመን ተጠያቂ መሆናቸውን ተረድተውና ኃላፊነት ተሰምቷቸው፣ በማስተዋል ማገልገል ይኖርባቸዋል:: «እያንዳንዳችን ስለ ራሳችን ለእግዚአብሔር መልስ እንሰጣለን» (ሮሜ 14:12:)::

መሪዎችን በእግዚአብሔር ፊት የሚያስጠይቃቸው ትልቅ ኃላፊነት የሚያገለግሏቸው ሰዎች ነፍስ ጉዳይ ነው:: በዕብ 13:17 «ለዋኖቻችሁ ታዘዙና ተገዙ፤ እነርሱ ስሌትን እንደሚሰጡ አድርገው በደስታ እንጂ በሀዘን እንዳያደርጉት ይህ የማይጠቅማችሁ ነበርና ስለ ነፍሳችሁ ይተጋሉ»[28] ይላል:: «በብርቱ የሚያስጠይቃቸው ነገር» የሚለው ቃል (ሐረግ) ስለሚያገለግሏቸው ሰዎች ነፍስ ከፍ ያለ ተጠያቂነት እንዳለባቸው ሲያመለከት ነው::

ስለዚህ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ተጠያቂነት ወደ ላይ ለእግዚአብሔር ወደ ጎን ደግሞ ለወንድሞቻቸው (ለምዕመናን) ነው:: ብዙውን ጊዜ ሰዎች ተጠያቂነት የማይወዱት የተጠያቂነት አሠራር መጽሐፍ ቅዱሳዊ ስላልሆነ ሳይሆን ተጠያቂነት ለሥልጣን አጠቃቀም፣ ለጊዜ፤ ለገንዘብና ንብረት አያያዝ ወሰን (ገደብ) ስለሚያበጅባቸው ነው::

አንድ ሰው በበላይነት በሚመራው ድርጅት ውስጥ እርሱ በቀጥታ ለሚያከናውነው ተግባር ብቻ ሳይሆን በድርጅቱ ውስጥ ለሚፈጸመው ነገር ሁሉ ተጠያቂነት አለበት:: መልካም ነገር ቢሆን ሊመሰገን፤ ክፉ ነገር ቢሆን ሊወቀስ ተጠያቂ ነው:: ስለሆነም በመሪነት ደረጃ ላለ ሰው የባለአደራነቱ አድማስ ሰፊ ነው::

[28] በአዲሱ መደበኛ ትርጉም «ለመሪዎቻችሁ ታዘዙ ተገዙላቸውም፤ ምክንያቱም እነርሱ በብርቱ የሚያስጠይቃቸው ነገር ስላለባቸው ስለ ነፍሳችሁ ጉዳይ ይተጋሉ» ይላል::





## 5.2 የጊዜ አጠቃቀም

ባለአደራነት «አላቂ» የሆኑ ዕቃዎችን ሁሉ በአግባቡ መጠቀምን ስለሚያጠቃልል ከዚህ ውስጥ የጊዜ አጠቃቀም ዋናው ነው:: ጊዜን ማስተዳደር የሚችል ሰው እግዚአብሔር ለዚያ ዘመን ያለውን ሀሳብ ተረድቶ በወቅቱ ያንን ሀሳብ አገልግሎ የሚያልፍ ሰው ነው::

የመሪን ጊዜ ፈላጊው ብዙ ነው:: ለራሱ ጊዜ ያስፈልገዋል፤ ቤተሰቡ ጊዜውን ይፈልገዋል፤ የአገልግሎት (ሥራ) ቦታው ሰፊ ጊዜ ይፈልጋል:: መሪው ካለው የአመራር ደረጃ ጋር በተያያዘ ብዙ በርካታ ተዛማጅ ሥራዎችና አገልግሎቶች ይኖራሉ:: አስቸኳይ ጉዳዮች ደግሞ ቀዳሚነትን ይጠይቃሉ:: ራሱን የሚያስተዳድር መሪ ጊዜውን ማስተዳደርና ለተግባሮችና ኃላፊነቶች ቅደም ተከተል መስጠት የሚችል ሲሆን ነው:: አንዱ እንዳለው «ፍሬያማነት 90 በመቶ ጊዜ አጠቃቀም ነው::»[29]

እያንዳንዱን ቀን በአግባቡ የሚጠቀምበት ሰው ፍሬያማ ሕይወት ይኖረዋል:: ለዕድሜ መጠንቀቅ ለደቂቃዎች ከመጠንቀቅ ይጀምራል:: የሰው ዕድሜ የዓመታት ድምር ነው፤ ዓመትም የወራትና የቀናት፤ ቀን የሰዓታት፤ ሰዓትም የደቂቃዎች:: ደቂቃዎችን ሳይቀር በአግባቡ ለመጠቀም የሚያቅድ ሰው ፍሬያማ ዕድሜ ለመኖር የወሰነ ሰው ነው::

ፍሬያማ የሆነ ዕድሜ መኖር ማለት ዘወትር በሥራና በእንቅስቃሴ ላይ መሆን ማለት አይደለም:: ሁልጊዜ እረፍት የሌለው ስራተኛ መስሎ መታየት በራሱ የጥሩ ጊዜ ተጠቃሚነት አመልካች አይሆንምና:: ጊዜን በአግባቡ መጠቀም ማለት ግን አስቀድሞ

[29] «success is ninety percent time management» Carl F. George and Robert E. Logan (1996), Leading and Managing Your Church, Fleming H. Revell, Grand Rapids, p.40.

የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደሆነ ማወቅና ያንን ለማከናወን መትጋት ነው:: ይህም ዘመኑን መዋጀት ነው (ኤፌ 5:16)::

ስለዚህ የጊዜ አጠቃቀም ባለአደራነትን የመወጣት አንድ መለኪያ ይሆናል:: ለዓላማው ጽኑ የሆነ ሰው የተሰጠውን ዕድሜና ዘመን ለተገለጠለት የእግዚአብሔር ፈቃድ አገልግሎት ያውለዋል::

ጊዜ ለሰው ልጆች የተሰጠ የከበረ ሀብት ነው:: በጥቅም ላይ ያልዋለና የባከነ ጊዜ አይመለስም:: የባከነ ጊዜ የሚካካሰው ለሌላ ተግባር ሊውል የሚችልን ጊዜ በመጠቀም ነው::

ጊዜን የፈጠረ እግዚአብሔር ከጊዜ ውጭ የሚኖር አምላክ ነው:: ፈቃዱን በሰዎች በኩል የሚያደርገው በጊዜ ውስጥ ስለሆነ የእርሱን ሰዓትና አሠራር ማወቅ ታላቅ ማስተዋል ነው:: እግዚአብሔር የሚቸኩልበትን ጊዜ አውቆ አብሮ መቸኮል ይገባል:: ሕዝብን ነጻ የማውጫ ሌሊት ሲሆን ማዳኑን ለመቀበል ተዘጋጅቶ መጠባበቅ ያስፈልጋል:: «ወገቦቻችሁን ታጥቃችሁ፤ ጫማችሁን በእግራችሁ፤ በትራችሁንም በእጃችሁ አድርጋችሁ እንዲህ ብሉት፤ ፈጥናችሁም ትበሉታላችሁ፤...» (ዘጸ 12:11) እንደተባለው ነው:: ሥራን ብቻ ሳይሆን መብልንም በፍጥነት መጨረስ የሚያስፈልግበት ጊዜ አለ::

ተስፋ የተሰጠው ሕዝብ የተስፋው ሙላት የሚፈጸምበትን ‹በዓለ ኀምሳን› በጸሎት መጠባበቅ ይገባዋል (ሐዋ 1፤2):: እንዲሁም ከምርኮ የመመለሻውን ሰባ ዓመት አስተውሎ በጾምና በጸሎት ወደ እግዚአብሔር የቀረበው ዳንኤል (ዳን 9)፤ የተሰጠውን ሥራ እስኪጨርስ ድረስ «ፀሐይ ትቁም» ያለው ኢያሱ (ኢያ 10:12-13) የዘመንንና የጊዜን ምንነት የተረዱ ነበሩ::

ስለዚህ ለዕድሜያችን ወሰን፤ ለጉብዝናችንም ወራት ገደብ ስላለው ቀን ሳለ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በማድረግ የተሰጠንን ራእይና






ተግባር እንደ ነህምያ ሌትና ቀን በመስራት በአጭር ጊዜ መጨረስ (ነህ 6:15) እንጂ በውጥን እንዳንተወው መትጋት አለብን::

ጊዜን በአግባቡ ስለመጠቀም ስናነሳ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከወንጌል መስፋፋትና ከእግዚአብሔር መንግሥት መስፋት ጋር በቀጥታ ላልተያያዙ ጉዳዮች የሚያውሉት ጊዜ ሁሉ ጊዜን በከንቱ እንደ ማባከን መሆኑን ማጤን ይገባል:: ለምሳሌ በአብያተ ክርስቲያናት መካከል የሚኖር ሙግት፤ በመሪዎች መካከል የሚኖር ‹ወንበሩ ይገባኛል› የሚሉና መሰል ክርክሮች ሁሉ ከዋናው የቤተ ክርስቲያን ትኩረት አቅጣጫ ውጪ የሆኑ የጊዜ ነቀዞች ናቸው:: እንዲህ ዓይነት ሁኔታ ባለበት መጨረሻው «መከሩ አልፎአል፤ በጋው ሄዶአል፤ እኛም አልዳንም» (ኤር 8:20) ይሆናል::

# ዓምድ 6:- አገልጋይነት:-

አገልጋይነት:- እግዚአብሔርን በመታዘዝ ሌላውን መጥቀም ነው:: ሐዋርያው ጳውሎስ «ከሰው ሁሉ አርነት የወጣሁ ስሆን የሚበልጡትን እንድጠቅም እንደ ባሪያ ራሴን ለሁሉ አስገዛለሁ» (1ቆሮ 9:19) እንዳለው የአገልጋይነት ትኩረቱ የሕዝብ መጠቀም ነው::




ስለ አገልጋይነት ቀደም ሲል በቅጽ 1 በስፋት የተመለከትን ሲሆን አሁን በመሪነት ሕንጻ አምድነቱ እናያለን:: ይህንን ለመገንዘብ መሪነት የሚፈለገው ለምን ዓላማ ነው? የሚለውን ጥያቄ በመመለስ እንጀምር::






ሰዎች መሪነትን የሚፈልጉበት ዓላማ ሁለት አቅጣጫ ሊኖረው ይችላል::

1. ቀዳሚው ትኩረት ማገልገል ሆኖ - በማገልገል መምራት
2. ቀዳሚው ትኩረት መገልገል ሆኖ - በመገልገል መምራት

በሁለቱ መካከል ትልቅ ልዩነት እንዳለ ማስተዋል ይገባል::[30] የመጀመሪያው አንድ ሰው የመሪነቱን ቦታ በመሠረቱ የሚፈልገው ለአገልግሎት ነው:: ለማገልገል የሚመጣ ሰው የመሪነቱን ቦታ የሚፈልገው አገልጋይ ለመሆን፤ ሕዝብን ለመጥቀም ነው:: የዚህ ሰው ትኩረት ያለው በሚሰጠው አገልግሎት ላይ ይሆንና የመሪነቱ ቦታ የአገልግሎት ሸክሙን (ጥማቱን) የሚፈጽምበት ስፍራ ይሆንለታል:: የሚያገለግለው በመምራት ይሆናል:: እንዲህ ባለ አገልጋይነት ልብ የመጣ መሪ የአገልጋይነት መንፈስ ያለው ትኩረቱ ማገልገል ይሆንና ቦታው የመሪነት ይሆናል::

ሁለተኛው አቅጣጫ ደግሞ አንድ ሰው ወደ መሪነት መምጣት የሚፈልገው መሪ መባልን ከመውደድ ነው:: ይህ ሰው የመጀመሪያው ትኩረቱ የመሪነቱን ስፍራ መጨበጥ ይሆናል:: ይህ ምኞት አብዛኛውን ጊዜ አገልጋይነትን ሳይሆን ከፍ ያለውን ሥልጣን መፈለግን (ወይም ገዥነትን) ያመለክታል:: እንዲህ ባለ ቅደም ተከተል «የአገልጋይነቱ ሸክም የሚመጣው የመሪነቱ ቦታ ከተያዘ በኋላ ነው» ብሎ እንደማሰብ ነው:: ስለሆነም ሰውየው «በገዥነቱ» የሚዋጥ ስለሚሆን አገልጋይነቱ ጨርሶም ላይመጣ ይችላል:: የገዥነቱ ምኞት ቀዳሚ ትኩረት ለሆነለት ሰው ዝቅ በማለት ለማገልገል ይከብደዋል::

[30] «The servant-leader is servant first ... It begins with the natural feeling that one wants to serve, to serve first.» taken from Servant Leadership: A journey into the nature of Legitimate Power and Greatness by Robert K. Greenleaf 1991, Ibid. p.1182.



መጣበቅ
መጠራት
ባለራእይነት
ታማኝነት
ባለአደራነት
አገልጋይነት
1
2
3
4
5
6
እግዚአብሔር መሪ፣
እግዚአብሔር እረኛ

የአገልጋይ መሪነት ዋናው ምሳሌያችን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: «የሰው ልጅ ሊያገለግልና ነፍሱን ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም» (ማር 10፡45)[31] አለ::

ጌታ ኢየሱስ ወደ ምድር የመጣው የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ ነው:: እርሱ ጌታ ነው፤ የመጣው ለማገልገል ነው:: ኢሳይያስ ስለ ጌታ ኢየሱስ «በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ ሕመማችንንም ተሸከሞአል እኛ ግን እንደ ተመታ በእግዚአብሔርም እንደ ተቀሠፈ እንደ ተቸገረም ቆጠርነው እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቆሰለ ስለ በደላችንም ደቀቀ» (ኢሳ 53፡4) በማለት ተንብዮአል:: እንዲሁም «በእርሱ ቁስል እኛ ተፈወስን» ይላል:: ጌታ የሰውን ዘር ሕማም[32]፤ ደዌ ተሸከመ:: ጌታ የቆሰለው ስለ እኛ መተላለፍ ነው:: እርሱ መተላለፍን አያውቅም:: የደቀቀው ስለ እኛ በደል ነው:: እንዲሁ በእርሱ ቁስል እኛ ተፈወስን::

እኛ ማለትም ሰዎች ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው በሆነው በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መከራ እንዴት እንደተጠቀምን እናስተውል:: የተጠቀምነው እኛ ነን:: የተጎዳው ወይም መከራ የደረሰበት እርሱ ነው:: እርሱ ጌታ ሆኖ እያለ ለባሪያዎቹ ለሰው ዘር ራሱን ለመስቀል ሞት አሳልፎ ሰጠ:: እኛን ለመጥቀም:: ይህ አገልጋይ መሪነት ነው:: እርሱ መሪ ነው፤ መሪነትን የሚፈጽመው የሚመራቸውን በማገልገል፤ እነርሱን በመጥቀም ነው::

በተመሳሳይ መንገድ ጌታ ኢየሱስ የደቀ መዛሙርትን እግር ያጠበበት ሁኔታ (ዮሐ 13፡1-17) ስለ አገልጋይ መሪነት በእጅጉ

[31] አዲሱ መደበኛ ትርጉም ነው «የሰው ልጅ ሊያገለግልና ሕይወቱን ለብዙዎች ቤዛ አድርጎ ሊሰጥ መጣ እንጂ ሊገለገል አልመጣምና»

[32] Suffering





ያስተምራል:: ጌታ ኢየሱስ መምህር ሆኖ ሳለ የደቀ መዛሙርትን እግር ዝቅ ብሎ በማጠቡ ስለ መሪ-አገልጋይነት በተግባር አስተምሯል:: ምሳሌነቱንም እንድንከተል ታዘናል:: ምሳሌነቱም የሚያሳየን መሪዎች ራሳቸውን ዝቅ በማድረግ የሚመሯቸውን ሰዎች ማገልገል እንዳለባቸው ነው:: «እኔ ጌታና መምህር ስሆን እግራችሁን ካጠብኩ እናንተ ደግሞ እርስ በርሳችሁ እግራችሁን ትተጣጠቡ ዘንድ ይገባችኋል» (ቁ.14) አላቸው:: «እኔ ለእናንተ እንዳደረኩ እናንተ ደግሞ ታደርጉ ዘንድ ምሳሌ ሰጥቻችኋለሁና» (ቁ.15) ብሏል::

መሪዎች አገልጋዮች በሆኑባቸው ድርጅቶች ወይም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሰዎች ወደ ጌታ ያድጋሉ፤ ጤናማ ሕይወት ይኖራቸዋል:: እነርሱ የሚያሳድጓቸው ሌሎች አገልጋዮች የአገልጋይነት ባሕርይ የያዙ ይሆናሉ:: በአንጻሩ የገዥነት ስሜትን ይዘው ወደ ሥልጣን የሚመጡ መሪዎች ባሉባቸው ቤተ ክርስቲያኖች «ታዳጊዎቹ አገልጋዮች» ከእነርሱ በላይ ያሉትን «ገዥዎች» አገዛዝ በመከተል እነርሱም «ትንንሽ ገዥዎች» ሆነው ያድጋሉ:: ስለሆነም ከአንድ መሪ ሥር ያሉ የሌሎች «አዳጊ አገልጋዮች/ መሪዎች» አስተዳደግ ከበላያቸው ያለውን መሪ ባሕርይ ለመመዘን ይረዳል::

ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች በላከው መልእክት ስለ ጢሞቴዎስ «እንደ እርሱ ያለ ስለ ኑሮአችሁ በቅንነት የሚጨነቅ ማንም የለኝምና ሁሉ የራሳቸውን ይፈልጋሉና የክርስቶስ ኢየሱስን አይደለም» (ፊሊ 2፡20-21)[33] ይላል:: ከዚህ ንግግሩ ሐዋርያው ጳውሎስ የሚያውቃቸው ወይም ከእርሱ ጋር ለማገልገል የጀመሩ ሌሎች አገልጋዮች እንደ ነበሩ ያመለክታል:: ሆኖም እንደ ጢሞቴዎስ ስለ ፊልጵስዩስ ሰዎች ከልቡ የሚገደው ሰው

[33] በአዲሱ መደበኛ ትርጉም ፊል 2፡20-21 «ስለ እናንተ ደኅንነት ከልቡ የሚገደው እንደ እርሱ ያለ ማንም የለኝም፡፡ ሁሉም የኢየሱስ ክርስቶስን ሳይሆን የራሳቸውን ፍላጎት ለማሟላት ይሯሯጣሉና»

አልነበረም:: ይህ የአገልጋይነት ባሕርይ ነው:: ሌሎችን ለማገልገል የሚያስብ ስለ ሌሎች መጽናትና ማደግ የሚገደው ሰው ነው:: አገልጋይነት - ሌላውን መጥቀም፤ መርዳት፤ ማሳደግ ነው (ማቴ 20:26-28፤ ማር 10:45፤ ሉቃ 22:24-27፤ ዮሐ 13:12-17)::

ከዚሁ ጋር አብሮ ልብ ማለት የሚያስፈልገው «...የራሳቸውን ይፈልጋሉና የክርስቶስ ኢየሱስን አይደለም» (ቁ.21) የሚለው ነው:: የክርስቶስ አገልጋይ የሚል ስያሜ ተሸክሞ የክርስቶስን ሳይሆን የግሉን ጥቅም የሚፈልግና የራሱን ፍላጎት ለማሟላት የሚሯሯጥ ሰው «የራሱ አገልጋይ» ነው:: ይህ የመሪነትን ስፍራ ለገዥነት የሚፈልግን ሰው ባሕርይ ያመለክታል::

በአገልግሎቱ የክርስቶስ የሆነውን የሚፈልግ ደግሞ የአገልጋይ መሪ ምሳሌ ነው:: አገልጋይ መሪ ስለሚያገለግላቸው ሰዎች የሚገደውና የክርስቶስ ኢየሱስን ሀሳብ ለማገልገል የሚሮጥ ሰው ነው:: መሪነት የሚመራውን ሕዝብ ለማገልገል «ዕድል» ማግኘትና ኃላፊነትን መሸከም እንጂ ከሚመሩት (ከሚገለገሉት) ሰዎች ጥቅም ለማግኘት የሚደረግ ገዥነት አይደለም::


በመንፈሳዊ መሪነት:- የሚመራ ሰው የበታው መጠሪያ መሪ ነው፤ ተግባሩ መምራት ነው፤ መሪነትን የፈለገው ሌሎችን ለመጥቀም ነው፤ አፈጻጸሙ በማገልገል ነው:: የቃሉ አስተማሪ የሆነ ሰው መምህር ነው፤ ተግባሩ ማስተማር ነው፤ አፈጻጸሙ በትሕትና ነው:: ትንቢትን የሚናገር ሰው ስጦታው ትንቢትን መናገር ነው፤ ተግባሩ የእግዚአብሔርን መልእክት ማስተላለፍ ነው፤ አፈጻጸሙ ሌሎችን ለማነጽ በፍቅር ነው (1ቆሮ 13):: እንግዲህ መሪነት ትልቁ ትንሹን የሚያገለግልበት፤ ብርቱው ደካማውን የሚደግፍበት አገልግሎት ነው:: ይህም ትሕትናን ይጠይቃል::





«አገልጋይ መሪ» ማለት መሪነቱን ለሌሎች ያስረከበና «ዝቅተኛ» ቦታን የመረጠ ማለት አይደለም:: ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የደቀ መዛሙርትን እግር ለማጠብ ሲነሣ «እኔ ጌታና መምህር ስሆን» ነው ያለው:: ያን ጊዜ እየሠራ የነበረው እግርን የማጠብ ተግባር «ዝቅተኛ» ሥራ ነው:: በዚያን ሰዓት እርሱ ጌትነቱን አልተወም፤ መምህርነቱንም አልጣለም:: እግር እያጠበ እያለ ጌታ ነው፤ መምህር ነው:: እግራቸውን በማጠብም ላይ እያለ እያስተማራቸው ነበር:: በጌትነቱና በመምህርነቱ ቀጥሏል::

የመሪ ጠላቱ መታበዩ ነው:: ዖዝያን ከሥልጣን እንደተባረረውና እንደተዋረደው (2ዜና 26:20-21) «ትዕቢት ከመጣች ውርደት ትመጣለች» (ምሳ 11:2):: መታበይ «እኔ» ብሎ ራስን ማኩራራት፤ ማዳነቅ፤ መሾምና ማሞገስ ነው:: እርሱ ባይኖር ሰማይ ይወድቅ ይመስል «እኔ ከሌለሁ ... ብሎ» ሰማይን በክንዱ ደግፎ እንደቆመ ሰው መምሰል ነው:: «ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉም» (ዮሐ 15:5) ያለ ጌታ ኢየሱስ ብቻ ነው::



በአጠቃላይ መሪነት ያለ ትሕትና መሠረቱ ሊሸከመው እንደማይችለው ሕንጻ ግንባታ ነውና ይዘምማል፤ ይወድቃል:: ለረጅም ሕንጻ ጠልቆ የተቆፈረ መሠረት እንደሚያስፈልግ ሁሉ ከሰይጣን አሽከላ ለማምለጥና በአገልግሎት ለማደግ የትሕትናን መጎናጸፊያ ሁልጊዜ መልበስ ይገባል::

ክርስቲያናዊ መሪነት ባሕርይና ችሎታ አስፈላጊዎች መሆናቸውን በቅጽ ሁለት በስፋት ተመልክተናል:: ባሕርይና ችሎታ በአንድነት

ተጣምረው የሚገለጹት በአገልጋይነት ነው:: ሁለቱን የሚያጣምር ደግሞ ትሕትና ነው:: ይህን በስዕላዊ መግለጫ እንመልከት::


ለክርስቲያናዊ መሪ ባሕርይና ችሎታ የመሰላል ሁለት ቋሚዎች ናቸው ማለት ይቻላል:: ሁለቱን ቋሚ እንጨቶች በማገናኘት ወደ ሰማይ የሚደርስ መወጣጫ የሚያደርጋቸው ሁለቱን የሚያይዛቸው አግዳሚ እንጨት ሲኖር ነው:: ሁለቱን የሚያያይዘው ትሕትና ማለትም «አገልጋይነት» ነው:: አገልጋይነት በሌለበት መረጋገጫ የሌለው ቋሚ እንጨት ብቻ መሆን ነው::

ስዕሉ ባሕርይና ችሎታ በአገልጋይነት እንዴት እንደሚጣመሩ ያሳያል:: በትሕትና የተያዘ መልካም ባሕርይና ችሎታ በጸጋና በአገልግሎት ወደ ላይ እያደገ የሚዘልቅ አገልጋይ መሪነት ነው::





# ዓምድ 7፡- አንድነት




ክርስቲያን መሪዎች ብዙ ቢሆኑም ሁሉም በመልካሙ እረኛ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥር የሚያገለግሉ «ትንንሽ» እረኞች ናቸው:: ኢየሱስ ክርስቶስ የእረኞች ሁሉ አለቃ ነው:: የዚህ እረኛ በጎች ሁሉ ባሕርያቸው አንድ ነው:- ይህም የክርስቶስ ባሕርይ ነው:: በጎቹ የእግዚአብሔር ቤተሰቦች ስለሆኑ አንድ አባት «አብ» አላቸው:: ሁሉም ከመንፈስ ቅዱስ ስለ ተወለዱና አንዱን መንፈስ ስለ ጠጡ በውስጥ ማንነታቸው «አንድ» ናቸው:: ስለዚህ የመንፈስ አንድነትን መጠበቅና በኅብረት መሥራት የማንነታቸው ክፍል ነው::

## 7.1 የመንፈስ አንድነትን መጠበቅ፤

መንፈሳዊ አንድነት የሰው ሥራ አይደለም:: መንፈሳዊ አንድነት የተመሠረተው በሰማይ ነው:: የእውነተኛ መንፈሳዊ አንድነት መተዳደሪያ ደንብ (ኮንስቲቲዩሽን) የተዘጋጀው፤ የጸደቀው በሰማይ ነው:: ስለዚህ ሕጉ ሰማያዊ ነው፤ ዘላለማዊ ነው:: ይህ አንድነት አይሻሽልም:: ከአንድ አገር፤ ከአንድ ወገን ከአንድ ዘመን ያለፈ በዓመታት ሁሉ ያሉትን የሚያጠቃልል አንድነት ነው::

ክርስቲያኖች ምንም እንኳን በቆሮንቶስ፣ በአንጾኪያ፣ በኢየሩሳሌም፣ በሮም በመኖራቸው የቦታ ርቀት፤ የዘርና የቋንቋ ልዩነት ቢኖራቸውም ሁሉም በአንዱ መንፈስ ወደ አንዱ አካል የተጠመቁ ናቸው (1ቆሮ 12:13):: በሮም ያሉ ክርስቲያኖች በኢየሩሳሌም ላለችው ቤተ ክርስቲያን ክፍል ናቸው (ሮሜ 12:5)::

የመንፈስ አንድነት ባለበት ሰላም አለ:: «በመስቀሉ ደም ሰላም አድርጎ ...» (ቆላ 1:19-20) እንደሚል ሰላምን የሚሰጥ የክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ነው:: ኅብረትና አንድነት እውነተኛ በሆነበት ሰላም አለ:: ምክንያቱም የመስቀሉ ደም ሰላምን ያደርጋል፤ የተጣሉትን ያስታርቃል፤ ልዩነትን ያጠፋል:: ምዕመናን «በሰላም ማሰሪያ» (ኤፌ3:4) እርስ በርስ መያያዝ ይገባቸዋል:: በቤተ ክርስቲያን (በአማኞች) መካከል መከፋፈል ሲኖር ያቺ አካል ታማሚ ትሆናለች:: የክርስቶስ ምስክር መሆን ያቅታታል::

ልዩነትን ካሰብን ግሪክ እና አይሁዳዊ - (የዘር)፣ የተገረዘ ያልተገረዘ - (የወገን)፣ አረማዊና እስኩቴስ - (ባሕላዊ)፣ ባሪያና ጨዋ - (ማኅበራዊ) ልዩነትን ሊያሳይ ይችላል:: ክርስቶስ ኢየሱስ «አንድ አዲስ ሰው» ያደረገው ይህንን ልዩነትና መከፋፈል አጥፍቶ ነው:: ከሁሉም አንድ አካል ነው የሠራው:: ይህም በክርስቶስ የተፈጠረ አዲስ ሰው ነው (2:15)::






የክርስቲያናዊ መሪ ተግባር አንድነትን መመሥረት አይደለም:: የቅዱሳን የመንፈስ አንድነት የተመሠረተው በኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ በመሆኑ እንደ ገና አይመሠረትም:: የመሪው ኃላፊነት የመንፈስን አንድነት መጠበቅ፤ ማጽናት ነው:: ይህን ለማድረግ መሪ ቀዳሚ ምሳሌ ሊሆን ይገባል::

## 7.2 በኅብረት መሥራት፤

አንድ ብቻ የእግዚአብሔር መንግሥት እንዳለ የሚያውቅ መሪ «ትንንሽ ግዛቶችን» አያበጅም:: ባለበት ቦታና ዘመን ለአንዱ ለእግዚአብሔር መንግሥት ይሠራል::

ክርስቲያናዊ አመራር በኅብረት ነው:: ለክርስቲያን የተሰጠው ሩጫ ሁሉም ሯጭ አሸናፊ የሚሆንበት ስለሆነ የእርስ በርስ ውድድርና ሽቅድድም አያስፈልግም:: እንዲሁም ዓሣ ለማጥመድ ገና ያልተነካ ሰፊ ባሕር እያለ ከተጠመደው ውስጥ እንደገና ማጥመድ «ማገለባበጥ» እንጂ ለመንግሥቱ ምንም ትርፍ አያስገኝም::

ሰዎች የሚያበጁት በረት የተሰጧቸውን በጎች ለመጠበቅና ለመመገብ እንዲያመቻቸው እንጂ ለመለያየት መሆን አይገባውም:: እግዚአብሔር ያልለያቸውን በጎች ከሌሎች መሰል በጎች ጋር እንዳይገናኙ በአጥር (ግንብ) ለብቻ ዘግቶ «ማጎር» አይገባም:: በጎቹ የሚገኙበት ቦታ በቆሮንቶስ፤ በኢየሩሳሌም፣ በኤፌሶን እንዲሁም በአዲስ አበባ ቢሆኑም የቦታ ርቀት ሳይገድባቸው ሁሉም አንዱን መንፈስ ጠጥተዋልና፣ በአንድ በረት ውስጥ የሚኖሩ በጎች ናቸው፤ የሁሉም እረኛ አንድ ነውና::



የማያገናኙና የተዘጉ ትንንሽ በረቶች[34] የኅብረት አለመኖርን ያመለክታል


በማጠቃለል፡- በፍቅር ውስጥ አንድነት፤ መከባበር አለ፡፡ በኤፌሶን ያለው ጢሞቴዎስ፣ በቀርጤስ ያለው ቲቶ በዚህም ዘመን ባለህበት ቦታ ያለኸው አንተ፤ ኃላፊነታችሁ በአጠቃላይ በጎች ሁሉ የክርስቶስ እንደሆኑ በማወቅ ለሁሉም አንድ ትልቅ እረኛ (ዕብ 13፡20) እንዳላቸው በመገንዘብ የበጐችን ፍቅርና አንድነት መጠበቅ ነው፡፡

የመንፈሳዊ መሪዎች መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ መመዘኛ በኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ የተመሠረተውን የቅዱሳን አንድነት ለመጠበቅና በሰላም ማሰሪያ ለመያያዝ የሚያደርጉት ፈቃደኝነትና ትጋት ነው፡፡ አንድ መሪ ፍቅርንና አንድነትን የሚጠላ ከሆነ መንፈሳዊነቱ የቱ ላይ ነው? እንዲህ ያለው ክርስቲያናዊ መሪ ሊባልስ ይገባልን? ምክንያቱም የክርስትና ምልክቱ ፍቅር፤ እርቅ፤ መዋደድ፤ ሰላም፤ አንድነት፤ ወንድማማችነት ስለሆነ ነው፡፡

[34] ስዕሉ የተወሰደው- መልሳቸው መስፍን (1998)፤ አደራ፡- ጢሞቴዎስ ወጣቱ አደራ ጠባቂ፤ አንድነት ማተሚያ ድርጅት








አንድ መንጋ - እረኛውም አንድ (ዮሐ 10፡16)

ሕያው ቃሉ የሚለው «በሰላም ማሰሪያ የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ ትጉ»[35] (ኤፌ 4፡3) ነው፡፡ ይህን በመቃወም የቅዱሳንን አንድነት አለመፈለግ በክርስትና ስም ለገዛ ክብር መኖር ነው፡፡ ስለ ትዳር እንኳን «እግዚአብሔር ያጣመረውን ሰው አይለየው» (ማቴ 19፡6) ተብሎ የለምን!! የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንማ እንዴታ!!! የቅዱሳንን አንድነት የማይፈልጉ መሪዎች ሲኖሩ መንጋው ያመነታል፤ ልቡ ውጭውን ይመኛል፤ «የፍቅር ራብተኛ» ይሆናል፡፡ እንዲህ ዓይነት መሪዎች ግባቸው አጭር ነው - የራሳቸው ስም መጠራት፤ «የዝናቸው» መውጣት፡፡ ፍላጎታቸው ትንሽ ነው፡- ለሚኖሩባት አጭር ዕድሜ «አንቱ» መባል፡፡ አሠራራቸው በኃይል ነው፡- በማስፈራራት ላይ የተመሠረተ ገዥነት፡፡ የቅዱሳንን አንድነት የማይወድ የክርስቶስን ሞት የሚያከፋፋ ነው፡፡

[35]«Endeavouring to keep the unity of the Spirit in the bond of peace.» (KJV), «Through the peace that ties you together, do your best to maintain the unity that the Spirit gives»,GW. «Through the peace that ties you together, do your best to maintain the unity that the Spirit gives»,ISV.

# ዓምድ 8:- መተካት




የእግዚአብሔር የማዳን ዕቅድ የዘላለም ዕቅድ ነው:: እያንዳንዱ መሪ በተሰጠው ጸጋ መጠን በራሱ ዘመን ከእግዚአብሔር የዘላለም ዕቅድ ውስጥ ላለበት ዘመንና አካባቢ የተሰጠውን በታማኝነት አገልግሎ ማለፍ ይጠበቅበታል::

ይህ የእግዚአብሔር የዘላለም እቅድ በኢትዮጵያ ውስጥ ከሞያሌ እስከ መቀሌ እንደሚሄድ አውራ መንገድ እንቁጠረው:: መንገድ ሠራተኞቹ «በአንድ ትውልድ ዘመን» የሚሠሩት ርቀት ለምሳሌ ከኮምቦልቻ-ደሴ ያለውን ተራራማ ስፍራ ቢሆን ከአዋሳ-ሻሸመኔ እንዳለው ሜዳማ መንገድ እንዲሆንላቸው መጠበቅ አይኖርባቸውም:: እያንዳንዱ አካባቢ (ማለትም ዘመን) የራሱ ባሕርይ አለው:: የሠራተኞች ድርሻ ላሉበት አካባቢ በሚሆን የምሕንድስና አሠራር የተሰጣቸውን ርቀት በመጨረስ መንገዱን





ማገናኘት ነው:: እንዲሁ በአንድ ዘመን ያለ መሪ ከእርሱ የሚጠበቀው በደረሰበት ጊዜና ቦታ ከጌታው የተሰጠውን የሥራ መጠን (ኮንትራት) በሚፈለገው ጥራት ደረጃ ሠርቶ በመጨረስ ለሚቀጥለው ትውልድ ማስረከብ ነው:: የሚቀጥለው ትውልድ ደግሞ የመንገዱን ስፋት ጠብቆ በዚያው የሥራ ጥራት የተሰጠውን ርቀት መጠን ሠርቶ ለሚመጣው ያስረክባል:: የሥራው ባለቤትና ተቆጣጣሪ እግዚአብሔር በየዘመናቱ በሕያውነቱ ሥራውን ይመራል::

## 8.1 የእግዚአብሔር ሥራ አይቋረጥም::

ጌታ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ የነገራቸው «እኔም እናንተ ያልደከማችሁበትን ታጭዱ ዘንድ ሰደድኋችሁ፤ ሌሎች ደከሙ እናንተም በድካማቸው ገባችሁ» (ዮሐ 4:38) በማለት ነው:: ደቀ መዛሙርት ከመኖራቸው (ከመምጣታቸው) በፊት በመንግሥቱ እርሻ ላይ ሠራተኞች ነበሩ:: የብሉይ ኪዳን ነቢያትና በዕብራውያን 11 የምናያቸው የእምነት ሰዎች ሁሉ በየዘመናቸው በዚህ ሥራ ላይ የደከሙ ሰዎች ናቸው:: ደቀ መዛሙርቱ ፍሬውን ማየት (አዝመራውን መሰብሰብ) ጀመሩ::

ስለዚህ የእግዚአብሔር ሥራ ቀጣይነት እንዳለው የሚረዳ መሪ ባለበት ዘመን እንዳሰበው ብዙ ፍሬ ባያገኝ በታማኝነት አገልግሎ ያልፋል:: እንዲሁም በእርሱ ዘመን ጥሩ ጅማሬ ያለው ሥራ ከእርሱ ጋር እንዳይሞት ሌሎችን በመተካት አስቀድሞ ይዘጋጃል:: ይህም አደራን ለሚቀጥለው ሰውና ትውልድ ማስተላለፍ ነው::

ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ወንጌልን አደራ ከመስጠቱ በፊት አስተምሮታል፤ ወደ ተለያየ ቦታ በመላክ አገልግሎትን አለማምዶታል:: በሕይወቱም የእርሱን አካሄድና ኑሮ እንዲመለከት አብሮት እንዲሆን አድርጓል:: ስለዚህ ጢሞቴዎስ አደራን

የተቀበለው ከጳውሎስ የሰማውን ቃል ብቻ ሳይሆን በጳውሎስ ሕይወትም ያየውን የወንጌል ጉልበትም ጭምር ነው።
ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱን የጠራቸው ከእርሱ ጋር እንዲኖሩና እንዲልካቸው ነው። ከእርሱ ጋር በመኖራቸው ከእርሱ ተምረዋል፣ ከእርሱ አይተዋል። ያዩትንና የሰሙትን በአንድ ላይ መልእክተኛ ሆነው ላሉበት ትውልድ አድርሰዋል።

ጳውሎስ ጢሞቴዎስን የሚመክረው ለአገልግሎት የሚሾሙ ሰዎች «አስቀድመው ይፈተኑ» (1ጢሞ 3፡10) እንደሚል አደራ የሚሰጣቸው ሰዎች ተፈትነው የታዩ መሆን አለባቸው። አደራን የሚቀበሉ ሰዎች ረዘም ባለ ጊዜ ውስጥ በተግባር ተፈትነው መታየታቸው ወንጌል በአልታመኑ (በማይገቡ) ሰዎች እጅ ወድቆ እንዳይቀር ያደርጋል። ስለዚህ አደራ ተቀባዮቹን ጥንቃቄ በተሞላበት ሁኔታ ማዘጋጀት (ማሰልጠን) እንዲሁም ደረጃ በደረጃ ኃላፊነትን በመስጠት በብቃት መወጣታቸውን መፈተንና መከታተል ይገባል።

እንደ ሐዋርያው ጳውሎስ «ለእኔ መኖር ክርስቶስ ነው» የሚሉ እግዚአብሔር ዓላማቸው የሆነ ክርስቲያናዊ መሪዎች ሲኖሩ ከሥራቸው ብዙ ተከታዮች (ተለማማጆች) ይኖራሉ። ጳውሎስ ብዙ መሪዎችን በምሳሌነት ያሳደገ «አለማማጅና፤ አሳዳጊ» ሐዋርያ ነው።

በአንጻሩ እንደ ካህኑ ዔሊ ዓይነት መሪዎች ሲኖሩ ከእነርሱ በኋላ የሚተካቸው እስከማይኖር ድረስ የእግዚአብሔርን ቤት ያራቁታሉ። «ከቡንያን ዛፍ ሥር ምንም ነገር አይበቅልም»[36] እንደሚባለው ይሆናል። ዳሩ ሕያው እግዚአብሔር በኤሊ ዘመን ሳሙኤልን አሳድጓል። ርስቱን ለማላገጫ አሳልፎ የማይሰጥ እግዚአብሔር የገዛ ክንዱ ይህን ያደርጋል።

[36] <Nothing.grows under a Bunyan tree.>





## 8.2 መልካም ምሳሌነት

ተተኪን ማሳደግ መልካም አርአያ በመሆን ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ በተደጋጋሚ በምሳሌነት መኖሩን ይገልጻል፤ የሚያገለግላቸው ሰዎች እርሱን እንዲመስሉ ይመክራል፤ በመልእክቶቹም እንደሚከተለው ይጽፋል።

- «እኔ ክርስቶስን እንደምመስል እኔን ምሰሉ» (1ቆሮ 11፡1)።
- «ከእኔ የተማራችሁትንና የተቀበላችሁትን የሰማችሁትንም ያያችሁትንም እነዚህን አድርጉ፤...» (ፊል 4፡9)፡፤
- «እኛን ልትመስሉ እንዴት እንደሚገባችሁ ራሳችሁ ታውቃላችሁና፤ በእናንተ ዘንድ ያለ ሥርዓት አልሄድንምና፤» (2ተሰ 3፡7)።
- «...ከመጀመሪያ ቀን ጀምሮ፤ በትሕትና ሁሉና በእንባ ከአይሁድም ሴራ በደረሰብኝ ፈተና ለጌታ እየተገዛሁ ዘመኑን ሁሉ ከእናንተ ጋር እንዴት እንደ ኖርሁ እናንተው ታውቃላችሁ፤» (ሐዋ 20፡17-19)።


ለተተኪነት የሚዘጋጅ ሰው ጥሩ ተተኪ ሆኖ የሚያድገው ቃሉና ተግባሩ ተመሳሳይ ከሆነ አስተማሪ ምሳሌነትን ሲመለከት ነው። ትልቁ ምሳሌነት ደግሞ በእግዚአብሔር ጸጋ ክርስቶስን መስሎ ማሳየት ነው።

ተተኪን ለማዘጋጀት ጊዜና ትዕግሥት ይጠይቃል። ‹በፍጥነት መሄድ ከፈለግህ ብቻህን ሂድ፤ ረጅም ርቀት መሄድ ከፈለግህ ከሌሎች ጋር ሂድ› እንደሚባለው ሰውን ማለማመድ ለፍጥነት እርምጃ ላይመች ቢችልም ሥራው ቀጣይነት ኖሮት በስፋት እንዲዘልቅ ለማድረግ ግን አስፈላጊ ነው። ስለዚህ ለመተካት - ማሳደግ፤ ምሳሌ መሆን፤ ማስተማር፤ ማለማመድ ያስፈልጋል።

## 8.3 በቡድን መሥራት[37]

ተተኪዎች በአንድ ቀን ጀንበር ወደሚፈለገው ደረጃ እንደማይደርሱ ሊዘነጋ አይገባም:: ተተኪን ማዘጋጀት «ተሠርቶ ያለቀለትን» ሰው መወከል (ማሰማራት) ሳይሆን የሚተካውን ሰው «መሥራት» ነው:: ስለዚህ አደራን ማስተላለፍ አስቀድሞ ሰዎችን በመምረጥ ይጀምራል:: ከዚያም እርስ በርስ በመቀራረብ ጌታን ማዕከላዊ ያደረገና በእውነት ላይ የተመሠረተ የጋራ የሆነ ዓላማ እንዲኖር በማድረግ ማሳደግና ሥራን (አገልግሎትን) ማለማመድ ይጠይቃል:: ለዚህም መሪዎች ከሥራቸው ላሉ የአገልግሎት «ተለማማጆች» ሥራን በመስጠትና ኃላፊነትን በመወከል ማዘጋጀት ይገባል::

የሚከተለው ስዕል (ፎቶ)[38] በመጠኑም ቢሆን እንደሚያመለክተው ተተኪዎች የሚያድጉት የሚወዳቸው፣ የሚመግባቸውና ጊዜ የሚሰጣቸው ሲኖር ነው::



ጌታ ዓሣ አጥማጆችን ሰዎችን የሚያጠምዱ አድርጎ ሲለውጣቸው[39] አስቀድሞ አብረውት እንዲሆኑ አደረገ (ማር 3:13-14፣ ዮሐ 1:39-40)፣ ከዚያም ላካቸው (ማቴ 10:5-8፣ ሉቃ 10:1-11)፣ እንዲሁም አፈጻጸማቸውን ይከታተል ነበር (ሉቃ 10:17)፣ በዚህም ለተጠሩበት

[37] Team Building

[38] Electronically retrieved

[39] Transform





እንዲበቁ አስቻላቸው::[40] ክርስቲያናዊ አገልግሎት በውክልና የሚሰጣቸው ሰዎች ለክርስቲያናዊ መሪነት የተሰጠውን መስፈርት የሚያሟሉ (1ጢሞ 3:1-13)፣ ለሥራው ጥበብ ያላቸው (ዘጸ 16:21)፣ መንፈስ ቅዱስና ጥበብ የሞላባቸው (ሐዋ 6:3) ሊሆኑ ይገባል::

ከዚህ ጋር በተያያዘ ሌላ መዘንጋት የሌለበት ነገር ለተተኪነት ወይም አደራን እንዲቀበሉ የሚዘጋጁት ሁሉ እንደታሰቡት ባይሆኑስ? የሚለው ጥያቄ ነው:: ከጌታ ጋር ከነበሩት መካከል እንኳ ሳይቀር ይሁዳ ከዳተኛ ሆኗል:: በጳውሎስም ዘመን እስከ መጨረሻው መስመሩን ጠብቀው ያልሮጡ እንደ ዴማስ (2ጢሞ 4:10) ዓይነቶች ነበሩ::

ሌሎችን በአገልግሎት ማሳደግና አገልግሎትን ማካፈል በሚያካፍለው ሰው ላይ ያለውን ጸጋ አይቀንስበትም:: ቀደም ሲል በሌላ ምዕራፍ እንዳልነው አንድ የበራ ሻማ ሌላውን ሻማ ሲለኩስ የአብሪው ሻማ ብርሃን ወይም ኃይል እንደማይቀንስ ሁሉ በመንፈሳዊውም ዓለም ብዙዎች በአገልግሎት እንዲሰማሩ ማድረግ የመሪውን ጸጋም ሆነ ኃይል አይቀንስበትም:: ከሙሴ ለሰባዎቹ ሽማግሌዎች መንፈስ በተወሰደበት ጊዜ የሙሴን መሪነት ሞገስ፣ ኃይል፣ ተሰሚነት አልቀነሰበትም (ዘኁ 11:17)::

በመንፈሳዊው ዓለም ተተኪን ለማዘጋጀት የእግዚአብሔርን ምክር ማወቅን ይጠይቃል:: ሙሴ አፈ ትብ ባለመሆኑ (በኮልታፋነቱ) (ዘጸ 4:10) ማን ለመሪነት ይጠቁመዋል? ዳዊትንስ ታላላቆቹ እያሉ «በልጅነቱ» ማን ያስበዋል? ጢሞቴዎስን «በታናሽነቱ» ማን ያስበዋል? የሰውን ልብ የሚያውቅ እግዚአብሔር እንዲህ ዓይነት «በሰው ዓይን» የማይሞሉትን ሰዎች ሀሳቡን የሚያገለግሉ አደረጋቸው:: ይህ የእግዚአብሔር ምርጫና ማስቻል ነው::

[40] Enabling, empowering, developing people

እንዲሁም ክርስቲያናዊ መሪዎች ከእነርሱ ጋር የሚያገለግሉና የሚተኩአቸውን ሰዎች ሲያዘጋጁ በሚያዩት ብቻ ተወስደው እግዚአብሔር ያልመረጠውን እንዳይሾሙ ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባቸዋል::


በማጠቃለል:- ክርስቲያናዊ መሪ ሌሎችን የሚያሳድግና ለኃላፊነት የሚያበቃ ነው:: የተጀመረው ሥራ እንዳይቋረጥ ይልቁንም ከእርሱ በኋላ በስፋት እንዲቀጥል አድርጎ የሚዘጋጅ ነው:: እንደ ጌታ የተለያየ ባሕርይና ችሎታ ያላቸውን በመውሰድ ወደ መልካም መለወጥ[41] የሚችል ነው:: ስለሆነም ከራሱ ቦታ መልቀቅ ጋር ሥራው እንዳይዳከም የሚያስብ ሰው ገና አገልግሎት ላይ እያለ ለሌሎች አሠራርን በማሳየትና ኃላፊነትን በማካፈል ሥራውን ያለማምዳል::

[41] Transforming Leader





# ዓምድ ፱:- ታዛዥነት




ታዛዥነት በሌላው ስር መሆንንና የእርሱን ፈቃድ ማገልገልን መግለጫ መንገድ ነው:: ታዛዥነት እግዚአብሔር ሲጣራ «ባሪያህ ይሰማልና ተናገር» (1ሳሙ 3:9) በማለት ለመስማት መውደድና የሰሙትን ማድረግ ነው::

ጌታ ኢየሱስ «በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ፣ ጌታ ሆይ፣ ጌታ ሆይ፣ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም» (ማቴ 7:21) እንዳለው መታዘዝ በድርጊት የሚገለጽ እምነት ነው:: ፍቅርንና እምነትን በተግባር ማሳየት ማለት ነው:: በራሱ ዘመን የእግዚአብሔርን ሀሳብ ያገለገለው ዳዊት «አምላኬ ሆይ፣ ፈቃድህን ለማድረግ ወደድሁ፣ ሕግህም በልቤ ውስጥ ነው»

(መዝ 40:8) አለ:: ሳሙኤል እንዳለውም ለእግዚአብሔር መታዘዝ ለእርሱ ከምናቀርበው አገልግሎት ሁሉ ይበልጣል (1ሳሙ 15:22-23)::

ክርስቲያን መሪዎች የእግዚአብሔር ተከታዮችና የእርሱን ፈቃድ ፈጻሚ ባሪያዎች ስለሆኑ ለእርሱ ለዋናው መሪ ታዛዦች ሊሆኑ ይገባቸዋል:: መታዘዝ ጌታን የመውደድ መግለጫ ነው::

## 9.1 መታዘዝ የፍቅር መግለጫ ነው::

መታዘዝና መውደድ የተያያዙ ናቸው:: ጌታ ኢየሱስ «ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ» (ዮሐ 14:15) አለ:: እንዲሁም «ትእዛዜ በእርሱ ዘንድ ያለችው የሚጠብቃትም የሚወደኝ እርሱ ነው፤ የሚወደኝንም አባቴ ይወደዋል እኔም እወደዋለሁ ራሴንም እገልጥለታለሁ ...የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል፤ ...የማይወደኝ ቃሌን አይጠብቅም» (ዮሐ 14:21-24) በማለት አስተምሯል:: የእርሱን ቃል መጠበቅ ለእርሱ ያለንን ፍቅር የምንገልጽበት መንገድ ነው::

ለእግዚአብሔር መታዘዝ በረከት አለበት:: እግዚአብሔር አብርሃምን «የምድር አሕዛብ ሁሉም በዘርህ ይባረካሉ፤ ቃሌን ሰምተሃልና» (ዘፍ 22:18) ብሎታል:: ጌታ ኢየሱስ ሲያስተምር «ብፁዓንስ የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው የሚጠብቁት ናቸው» (ሉቃ 11:28) አለ:: እንዲሁም ሐዋርያው ያዕቆብ በመልእክቱ «...ነገር ግን ነጻ የሚያወጣውን ፍጹሙን ሕግ ተመልክቶ የሚጸናበት፤ ሥራንም የሚሠራ እንጂ ሰምቶ የሚረሳ ያልሆነው፤ በሥራው የተባረከ ይሆናል» (ያዕ 1:22-25) አለ::

አገልጋዮች የእግዚአብሔርን ፈቃድ በማድረግ የምንታዘዘው ለእርሱ የከበረና የምንጠቅም ዕቃ ለመሆን ነው:: እግዚአብሔር





እስራኤላውያንን «ቃሌን በእውነት ብትሰሙ ኪዳኔንም ብትጠብቁ፤ ...የካህናት መንግሥት የተቀደሰም ሕዝብ ትሆኑልኛላችሁ» (ዘጸ 19:5-6) ብሏቸው ነበር:: በአዲስ ኪዳንም «በትልቅም ቤት የእንጨትና የሸክላ ዕቃ ደግሞ አለ እንጂ የወርቅና የብር ዕቃ ብቻ አይደለም፤ እኩሌቶቹም ለክብር፤ እኩሌቶቹም ለውርደት ይሆናሉ፤ እንግዲህ ማንም ራሱን ከእነዚህ ቢያነጻ፤ ለክብር የሚሆን የተቀደሰም ለጌታውም የሚጠቅም ለበጎም ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ዕቃ ይሆናል» (2ጢሞ 2:20-21) ይላል:: እግዚአብሔርን መታዘዝ ለእርሱ መቀደስ፤ የእርሱ ወገን መሆንና፤ እርሱን ለማገልገል መለየት ነው:: መሪዎች የእግዚአብሔር ሀሳብ አገልጋዮች ስለሆኑ እርሱ የሚጠቀምባቸው የክብር ዕቃዎች እንዲሆኑ እግዚአብሔርን ከማያከብሩ ነገሮች መራቅ ይገባቸዋል::

እግዚአብሔርን የምንታዘዘው ጽድቅ ለማግኘት ወይም የጽድቅ ማሚያ ሥራ ለመፈጸም አይደለም:: ጽድቅ የእግዚአብሔር ጸጋ ስጦታ እንጂ በሥራ የሚገኝ አይደለምና:: «ጻድቅ በእምነት ይኖራል ተብሎአልና ...» (ገላ 3:11) የምንታዘዘው ስለ ጻደቅን ነው:: በነጻ ጽድቅን ስላገኘ ለክርስቲያን መታዘዝ ምስጋናውንና ደስታውን ለእግዚአብሔር የሚገልጽበት መንገድ ነው::

ስለዚህ ክርስቲያን መሪ እግዚአብሔርን መታዘዝ ያለበት ፈቃዱን በመፈጸም እርሱን ደስ ለማሰኘት ነው:: እግዚአብሔርን የሚታዘዝ ሰው ዓይኖቹ ያዩታል በፊቱም ሞገስ ያገኛል፤ የሚሠራውም ይከናወንለታል::

## 9.2 የሚታዘዝ በጥራትና በትጋት ይሠራል::

ጌታ እግዚአብሔር ሠራተኛ አምላክ ነው:: እግዚአብሔር መልካምን ነገር ይሠራል፤ እጅግ መልካም አድርጎ ይሠራል::

እግዚአብሔር ፍጥረትን በፈጠረ ጊዜ «ያደረገውን ሁሉ አየ እነሆም እጅግ መልካም ነበረ» (ዘፍ 1:31) ይላል።

ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆላስያስ ሰዎች በጻፈላቸው መልእክት «... የምታደርጉትን ሁሉ በትጋት አድርጉት» (ቆላ 3:23) ይላቸዋል። ለዚህም «ከጌታ የርስትን ብድራት እንደምትቀበሉ ታውቃላችሁና የምታገለግሉት ጌታን ክርስቶስን ነውና» (3:24) ይላል። እነዚህ ሰዎች ለሌሎች ሰዎች የሚሠሩ ሠራተኞች ቢሆኑም ጌታን የምታገለግሉ ናችሁ፤ ብድራትንም ከእርሱ ዘንድ ትቀበላላችሁ ይላቸዋል። ትጋት ሥራን በሙሉ ልብና በፍጥነት ማከናወን ነው።

በተጨማሪም «የሚበድልም የበደለውን በብድራት ይቀበላል» (ቆላ 3:25 እንዲሁም 2ጴጥ 2:13፤ 2ጢሞ 4:14)። በሥራ ላይ ልግመኛ የሆነ (ማለትም የሚገባውን ያህልና በጥራትና በትጋት ያልሠራ) ሰው ለልግመኛነቱ ብድራት ወይም ዋጋ ከጌታ እንደሚሰጠው ያሳያል። ሰው ሰውን በማገልገሉ ከጌታ ዘንድ ብድራት የሚያሰጥ ከሆነ ጌታ ክርስቶስን የሚያገለግል ሰውማ ምን ያህል ብድራት ይጠብቀው ይሆን?

አዎ እግዚአብሔርን መታዘዝ ከእግዚአብሔር ዘንድ ብድራት ያስገኛል። የእግዚአብሔርን ሥራ እንዴት እንደሠራን የሚፈተንበት የሚመዘንበት ቀን ወደፊት አለና። «እያንዳንዱ በሥጋው የተሠራውን በብድራት ይቀበል ዘንድ ሁላችን በክርስቶስ በፍርድ ወንበር ፊት ልንገለጥ ይገባናልና» (2ቆሮ 5:10)።

እግዚአብሔርን እየታዘዙ ፈቃዱን በጥንቃቄ የሚያገለግሉ በወርቅና በብር እንደሚሠሩ አናጺዎች ናቸው። «ማንም ግን በዚህ መሠረት ላይ በወርቅ ቢሆን በብርም በከበረ ድንጋይም በእንጨትም በሣርም ወይም በአገዳ ቢያንጽ፤ የእያንዳንዱ ሥራ ይገለጣል፤ በእሳት ስለሚገለጥ ያ ቀን ያሳያልና፤ የእያንዳንዱም ሥራ እንዴት መሆኑን





እሳቱ ይፈትነዋል። ማንም በእርሱ ላይ ያነጸው ሥራ ቢጸናለት ደመወዙን ይቀበላል፤ የማንም ሥራ የተቃጠለበት ቢሆን ይጎዳበታል፤ እርሱ ራሱ ግን ይድናል ነገር ግን በእሳት እንደሚድን ይሆናል» (1ቆሮ 3:14-15)።

እግዚአብሔርን ያገለገለ መስሎት ዕድሜ ዘመኑን ሙሉ ሲሯሯጥ ኖሮ በመጨረሻው ተመዝኖ መልካም ብድራት ሳያገኝ የሚቀር አገልጋይ እጅግ አሳዛኝ ነው። ይህ «እርሱ ራሱ ግን ይድናል ነገር ግን በእሳት እንደሚድን ይሆናል» (1ቆሮ 3:15) እንደተባለው ነው። ይህ እግዚአብሔር ደስ ያልተሰኘበት አገልግሎት ነው። ስለዚህ ክርስቲያናዊ መሪ ደስ የሚለው በመሪነት ስፍራ ስላለና ‹አገልግሎት ስለበዛለት› ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔርን ሥራ እርሱ በሚመርጠው መንገድና በጥንቃቄ መፈጸም ሲችል ነው።

ለእግዚአብሔር የሚቀርብ መሥዋዕት ሁሉ ንጹህና ነውር የሌለበት ሊሆን ያስፈልገዋል። እንዲሁም ‹እግዚአብሔርን እናገለግላለን፤ የእርሱ ባላደራዎች ነን፤ ሥራና ኃላፊነት ከእርሱ ተቀብለናል፤ የእርሱን ሥራ እንሠራለን› የሚሉ ክርስቲያን መሪዎች ሁሉ የሚሠሩት ሥራ ሁሉ በጥንቃቄ፤ በንጹህ ልብና በትጋት ሊሠሩት ያስፈልጋቸዋል። ቃሉ «የእግዚአብሔርን ሥራ በቸልታ የሚሠራ የተረገመ ይሁን» (ኤር 48:10) እንደሚል በእግዚአብሔር ሥራ ላይ ተሠማርቶ ስንፍና የሚያሳይ ሀኬተኛ የሆነ መሪ በእግዚአብሔር ዘንድ መጠየቁ አይቀርም። የሚሠራውንም በገለባና በሣር የሚገነባ አገልጋይ የራሱን ምኞት ያገለገለና ጌታን ያልታዘዘ ሰው ነው።


እንዲሁም በመንፈሳዊው ዓለም የአንድ አገልጋይ ትጋትና ውጤታማነት የሚመዘነው ከሌላ አገልጋይ ሕይወት አንጻር አለመሆኑን መገንዘብም ይጠቅማል። የእያንዳንዱ ታዛዥነትና ትጋት የሚታየው በተሰጠው መክሊት መጠን በማገልገሉ ነው።

አንድ ሰው ታላቅ ነገር አደረገ ቢባል እግዚአብሔር ካበዛለት ጸጋ የተነሳ መሆኑም መዘንጋት የለበትም:: አሥር መክሊት የተሰጠው በሰባቱ ቢሠራ በጣም ብዙ ሠርቷል እንላለን:: ከተሰጠው አንጻር ግን ይህ ሰው በጉድለት እየተመላለሰ ነው:: አምስት የተሰጠው በአራቱ ቢሠራ ከመጀመሪያው ይልቅ የበለጠ አከናውኗል:: አንድ የተሰጠው በአንዱ ቢሠራበት ከተሰጠው መክሊት አንጻር አገልግሎቱ ሙሉ ነው:: ስለዚህ በጣም ብዙ በማከናወናቸው «ታላቅ» የሚባሉ መሪዎች የሚሠሩት ሥራ ብዙ ሊሆን ቢችልም መመዘን የሚገባቸው ከተሰጣቸው መክሊት (ጸጋ) አንጻር ነው:: በተሰጠው መክሊት መጠን የሚያገለግል አገልጋይ ታዛዥና ትጉ ነው::





# ዓምድ 10:- ጽናት




ጽናት:- አንድ ሰው ከጌታ የተቀበለውን አገልግሎትና የተሰጠውን ተልዕኮ ለመጨረስ ክርስትና ሕይወት የሚጠይቀውን ትዕግስትና ዋጋ በመክፈልና እስከ መጨረሻ በመሮጥ ሩጫውን መጨረስ ነው::

ጽናት:- ዓላማን ትኩር ብሎ የማየት፤ የሚገኘውን ክብር የመውደድ፤ ወደ ዓላማ የመሮጥና እስከ መጨረሻው የመታገስ ድምር ውጤት ነው:: መጽሐፍ ስለ ጌታ ኢየሱስ ጽናት በመናገር እኛን ሲመክረን «...እኛ ደግሞ ሸክምን ሁሉ ቶሎም የሚከበንን ኃጢአት አስወግደን፤ የእምነታችንንም ራስና ፈጻሚውን ኢየሱስን ተመልክተን፤ በፊታችን ያለውን ሩጫ በትዕግሥት እንሩጥ፤ እርሱ

ነውርን ንቆ በፊቱም ስላለው ደስታ በመስቀል ታግሦ በእግዚአብሔር ዙፋን ቀኝ ተቀምጦአልና» (ዕብ 12፡1-3) ይላል፡፡ ስለዚህ ጽኑ ሰው ብድራቱን እስኪያገኝ ድረስ ጥሪው የሚጠይቀውን ዋጋ ለመክፈል የሚዘጋጅ ነው፡፡

ጽናትና ተስፋ የተያያዙ ናቸው፡፡ እግዚአብሔር የተናገረውን ተስፋ ሳይደከሙ በእምነት መጠበቅ ጽናት ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ አብርሃም ሲናገር «የመቶ ዓመትም ሽማግሌ ስለሆነ እንደ ምውት የሆነውን የራሱን ሥጋና የሣራ ማኅፀን ምውት መሆኑን በእምነቱ ሳይደክም ተመለከተ፤ ለእግዚአብሔርም ክብር እየሰጠ፤ የሰጠውንም ተስፋ ደግሞ ሊፈጽም እንዲችል አጥብቆ እየተረዳ፤ በእምነት በረታ እንጂ በአለማመን ምክንያት በእግዚአብሔር ተስፋ ቃል አልተጠራጠረም» (ሮሜ 4፡19-21) ይላል፡፡

ጽናት የተጀመረው መልካም ነገር እስኪፈጸም ድረስ በችግሮች አለመረታትን፤ ተግዳሮትንና ፈተናን ተጋፍጦ ማሸነፍን፤ በመከራ ታግሶ ዳር መድረስን ያጠቃልላል (ሮሜ 5፡3፤ 2ተሰ 1፡4)፡፡ ጽናት በእግዚአብሔር ፊት የከበረ ዋጋ አለው፡፡ «ወንድሞች ሆይ፤ የመከራና የትዕግሥት ምሳሌ የሆኑትን በጌታ ስም የተናገሩትን ነቢያትን ተመልከቱ። እነሆ፤ በትዕግሥት የጸኑትን ብፁዓን እንላቸዋለን፤ ኢዮብ እንደ ታገሠ ሰምታችኋል፤ ጌታም እንደ ፈጸመለት አይታችኋል...» (ያዕ 5፡10-11)። ዘማሪውም «እግዚአብሔርን ተስፋ አድርግ፤ በርታ፤ ልብህም ይጽና፤ እግዚአብሔርን ተስፋ አድርግ» (መዝ 27፡14) ብሏል።

ከክርስቲያናዊ መሪነት ጋር በተያያዘ መሪዎች ከሚጠበቅባቸው የጽናት መስመሮች ሦስቱን እንመልከት፡፡





## 10.1 ተግዳሮት ሲበዛ

እግዚአብሔር የሰጠው የሥራ ራእይ ከችግርና ተግዳሮት ነጻ ይሆናል ብሎ መገመት አይቻልም፡፡ ይልቁንም በመጽሐፍ ቅዱስ በተደጋጋሚ እንደሚታየው የእግዚአብሔር ሀሳብ ባለበት ተግባር ላይ ችግርና ተግዳሮት ይበረታል፡፡ ይህን ለመገንዘብ እንዲረዳን የነህምያን አመራር በጥቂቱ እንመልከት፡፡

ቀደም ሲል በቅጽ ፫ እንደተመለከትነው ነህምያ የኢየሩሳሌምን ቅጥር ለማደስ ሲነሣ ከውጭና ከውስጥ በተደጋጋሚ ከፍተኛ ተቃውሞና ችግር ደርሶበታል፡፡ ገና ከመነሻው ሕዘቡ ለማደስ በዝግጅት ላይ እያሉ ሰንባላጥ፤ ጦብያና ጌሳም በንቀት ሳቁባቸው፡፡ ለእነርሱ የንቀት ሳቅ የነህምያ መልስ «የሰማይ አምላክ ያከናውንልናል፤ እኛም ባሪያዎቹ ተነሥተን እንሠራለን» (2፡20) የሚል ነበር፡፡ እንዲሁም ጠላቶች እጅግ በመቈጣትና በብስጭት «እነዚህ ደካሞች አይሁድ የሚሠሩት ምንድር ነው? ...በድንጋይ በሚሠሩት ቅጥራቸው ላይ ቀበሮ ቢመጣበት ያፈርሰዋል» አሉ (4፡1-3)። ለዚህ ከፍተኛ ንቀት ደግሞ የነህምያ መልስ ወደ አምላኩ መጮህና በቅጥሩ ሥራ መበርታት ነበር (4፡4-6)፡፡

ተቃዋሚዎች ሥራው በመቀጠሉ እጅግ ተቈጡ፤ ኢየሩሳሌምን ለመውጋትና ለማሸበር ጠላቶች ሁሉ በአንድነት ተማማሉ። በዚህ ጊዜ ነህምያ «ወደ አምላካችንም ጸለይን ...ተጠባባቂዎች በሌሊትና በቀን አደረግን» (4፡9) አለ። ጠላቶቻቸው ሊወጓቸው እንደሚመጡ ሲሰማም «አትፍሩአቸው፤ ታላቁንና የተፈራውን ጌታ አስቡ» (4፡14) ብሎ ሕዝቡን አበረታታቸው፡፡ እግዚአብሔርም የጠላቶቻቸውን ምክር ከንቱ አደረገው፡፡

የሥራውን መግፋት ሲመለከቱ እነ ሰንባላጥ ተንኮል አስበው አንተና እኛ «እንገናኝ» ብለው ወደ ነህምያ ይልኩበት ጀመር፡፡ ይህንም በተደጋጋሚ አደረጉ፡፡ የነህምያ መልስ «...ትልቅ ሥራ

<u>እሠራለሁ፤ እወርድም ዘንድ አይቻለኝም፤ ሥራውን ትቼ ወደ እናንተ በመውረዴ ስለ ምን ሥራው ይታጐላል?</u>» (6:1-4) ብሎ መለሰላቸው::

ነህምያ በሥራው መጀመሪያ ላይ የኢየሩሳሌምን ሕዝብ ሰብስቦ ስለ ሥራው ገልጾላቸዋል:: ሕዝቡም «እንነሣና እንሥራ» (2:18) በማለት በሥራው ተሰማርተዋል:: ሆኖም የቅጥሩ ሥራ እኩሌታው ላይ ደርሶ እያለ (4:6) «የተሸካሚዎች ኃይል ደከመ፤ ፍርስራሹም ብዙ ነው፤ ቅጥሩንም እንሠራ ዘንድ አንችልም» (4:10) የሚለው የአይሁድ ማንጎራጎር ጽናትን በእጅጉ የሚፈታተን ነበር:: ይህ የሕዝቡ መሰላቸትና የውስጥ ችግር የጀመረው የግንቡ እድሳት በግማሽ ካለቀ በኋላ በመሆኑ ፍርስራሹ በግማሽ እንደሚቀንስ ይገመታል:: ይሁን እንጂ የዚህ የውስጥ ችግር ምክንያት ከሥራው ብዛት ይልቅ የመንፈስ መዛል ነበር:: እንደ ተነፈሰ የመኪና ጎማ የሆነን የሰው መንፈስ ማንሻው ‹ክሪክ› ምንድን ነው?

የውስጥ ችግር ማሸነፊያው መንገድ ከጸሎት በተጨማሪ፤ በሕዝቡ መካከል በመገኘት ማበረታትና በምሳሌነት መምራት (5:15) እንዲሁም ከሕዝቡ ጋር በመመካከር ችግርን መፍታት መሆኑን ከነህምያ እንማራለን::

ነህምያ በተደጋጋሚ ለቀረበለት የማባበያ ጥያቄ የሰጠውን መልስ በድጋሚ ልብ እንበል:: «ትልቅ ሥራ እሠራለሁ፤ እወርድም ዘንድ አይቻለኝም፤ ሥራውን ትቼ ወደ እናንተ በመውረዴ ስለ ምን ሥራው ይተጓጐላል?» የሚል ነበር:: በእግዚአብሔር ሥራ ላይ የተሰማራ ሰው ከሥራው የሚያዘናጋውንና የሚገዳደረውን ሁሉ በእግዚአብሔር ታምኖ በማስወገድ የተሰጠውን ኃላፊነት ዳር ማድረስ ይጠበቅበታል:: ዓይኑን በችግሩ ላይ የሚያደርግ ሰው ተሰርቶ የተጠናቀቀ ቅጥር ማሰብ ያዳግተዋል:: የእግዚአብሔርን





ትልቅነት የሚያስብ ግን ችግሩ ስለሚያንስበት በርትቶ ይሠራል፤ በተሰጠው ራእይ ላይ የተነሣበትን ተግዳሮትም በጽናት ያሸንፋል::

## 10.2 «አይዞህ» እና «እኔ ከአንተ ጋር ነኝ»

‹አይዞህ› የሚል ቃል በሥራ ለደከመና ፈተና ለበዛበት ሰው በበረሃ እንደሚገኝ ምንጭ ነው ማለት ይቻላል:: ‹አይዞህ› የሚለውን ቃል የሚሰማ ሰው ‹እጅህን አትስጥ›፤ ‹ቀጥል›፤ ‹ድል በፊትህ አለ› የሚል ትርጉም ስለሚሰጠው ጉልበት ያገኛል፤ ይበረታታል:: ይህ አይዞህ ቃል ከመለኮት ከመጣ ደግሞ ‹ኃይል› ይሆናል::

ጳውሎስ በአገልግሎቱ አይዞህ የተባለ ሰው ነበር:: ሰዎች ጳውሎን ለመግደል እጅግ በተነሳሱበት ሰዓት «በሁለተኛውም ሌሊት ጌታ በአጠገቡ ቆሞ ጳውሎስ ሆይ፤ በኢየሩሳሌም ስለ እኔ እንደ መሰከርህ እንዲሁ በሮሜም ትመሰክርልኝ ዘንድ ይገባሃልና አይዞህ አለው» (ሐዋ 23:21):: ከዚህ ልብን ከሚያጸና ቃል የተነሣ ጳውሎስ በረታ:: ቀሪውንም መንገድ «አይዞህ» ባለው ጌታ ታምኖ ቀጠለ:: እርሱም በተራው ሰዎችን «አይዞአችሁ» ይል ነበር:: «አይዞአችሁ ብዬ እመክራችኋለሁ፤ ይህ መርከብ እንጂ ከእናንተ አንድ ነፍስ እንኳ አይጠፋምና» (ሐዋ 25:11)፤ እንዲሁም «እናንተ ሰዎች ሆይ አይዞአችሁ፤ እንደ ተናገረኝ እንዲሁ እንዲሆን እግዚአብሔርን አምናለሁና» (25:25) አለ:: አዎ ሰዎቹ ተጽናኑ፤ እግዚአብሔርም ለጳውሎስ እንደተናገረው አደረገ::

ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ሲጽፍ «በእስያ ያሉቱ ሁሉ ከእኔ ፈቀቅ እንዳሉ ታውቃለህ...» (2ጢሞ 1:15) እንዳለው በችግር ጊዜ አብረው የማይቆሙ፤ ጉዞን አብረው የማይጨርሱ፤ አሳልፈውም እንኳ የሚሰጡ ቢኖሩ እግዚአብሔር ‹አይዞህ› ያለው ሰው ግን «የቀረውንም ነገር ሳልቆጥር፤ ዕለት ዕለት የሚከብድብኝ የአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ አሳብ ነው» (2ቆሮ 11:28) ይላል::

በአንድ ሰው ሕይወት እግዚአብሔርን የሚያከብር ታላቅ ነገር ለመከናወኑ ቁልፉ እግዚአብሔር ከዚያ ሰው ጋር መሆኑ ነው:: ጌዲዮን ራሱን ደብቆ ባለበት ሰዓት የእግዚአብሔር መልአክ «አንተ ጽኑዕ ኃያል ሰው» ሲለው ምክንያቱንም «እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ነው» (መሳ 6:12) በማለት ይነግረዋል:: ጌድዮን መልሶ «እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ይህ ነገር ሁሉ ለምን ደረሰብን? ...» (6:13) ማለቱ እግዚአብሔር አብሮ ሲሆን ተአምራት እንደሚሆን ጥበቃውም እንደሚበዛ ያለውን መረዳት ይገልጻል:: እስራኤልን ከጠላቶች እንዲያድን እግዚአብሔር ሲልከው ጌድዮን የታየው የእርሱ ታናሽነት ነበር:: «እግዚአብሔርም በእርግጥ ከአንተ ጋር እሆናለሁ፤ ምድያምንም እንደ አንድ ሰው አድርገህ ትመታለህ» (6:16) ባለው መሠረት ጌድዮን ሄዶ ገና ሳይገጥማቸው እግዚአብሔር በምድያም ሰፈር በሕልም ሥራውን ጀመረ (መሳ 7:13-15) ጠላቶችም ተሸነፉ::

በአንጻሩ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር የነበረ ሰው ሶምሶን ቃል ኪዳኑን ሳይጠብቅ ጸጉሩ ከተላጨ በኋላ «እወጣለሁ እንደ ወትሮውም ጊዜ አደርጋለሁ አለ። ነገር ግን እግዚአብሔር ከእርሱ እንደ ተለየው አላወቀም» (መሳ 16:20) ተብሏል::

ጽኑ ሰው በእግዚአብሔር የሚደገፍና ለሚያገኘው ድል ሁሉ ክብርን ለእርሱ የሚሰጥ ነው:: «በክርስቶስ» የሚለውን ሳንጨምር «ከአሸናፊዎች እንበልጣለን» የሚለውን ብቻ በከፊል በመጥቀስ ‹አደረግሁት፤ አሸነፍሁት፤ ጣልሁት፤ ወዘተ.› ብንል ትልቅ ስህተት እናደርጋለን፤ ትዕቢት ይሆንብናል፤ ጠላታችንም ሊከስን ይጀምራል:: ቃሉ «በዚህ ሁሉ ግን በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን» (ሮሜ 8:37) እንደሚል ያገኘነው ድል የተገኘው የጠላትን ሥራ ባፈረሰው በክርስቶስ መሆኑን ካላወጅን በስተቀር ‹ወጥመዱን ሰባበርሁት› ብንል የራሳችን ጉብዝናና ‹ገድል›



መልካም እረኝነት ቅጽ ፬

ይመስልብናል:: ትክክለኛው «ነገር ግን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ድል መንሣትን ለሚሰጠን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን» (1ቆሮ 15:57፤ እንዲሁም 2ቆሮ 2:14) ማለት ነው:: ስለዚህ ለመንፈሳዊ ድል ሚስጥሩ እግዚአብሔር ከዚያ ሰው ጋር መሆኑ ነው::

የእግዚአብሔር ባሪያ ሙሴ ከሞተ በኋላ የእስራኤልን ሕዝብ እንዲመራና እግዚአብሔር ለአባቶቻቸው የሰጣቸውን ምድር ለሕዝቡ እንዲያወርስ የተሾመው ሰው ኢያሱ ነበር:: እግዚአብሔር ይህን ኃላፊነት ለኢያሱ ሲሰጠው ሦስት ጊዜ «ጽና» (ኢያ 1:6-9) ይለዋል:: ኢያሱ ከሙሴ ጋር የነበረና የሙሴ አገልጋይ ቢሆንም አሁን በፊቱ ባለው መንገድ የሚገጥመውን አያውቅም፤ ገና አላየውም:: በፊቱ ዮርዳኖስና ኢያሪኮ አሉ:: እንዲሁም በየስፍራው የሚገጥማቸውም በርካታ ጦርነቶች አሉ:: ስለዚህ እንዲጸና እግዚአብሔር ደጋግሞ ያዘዋል፤ ይመክረዋል፤ «አይዞህ»ም ይለዋል::

ኢያሱን «አይዞህ» ብሎ እንዲጸና የሚናገረው ሙሴን የመረጠ፤ ያለማመደና የመራ እግዚአብሔር ነው:: በሙሴ ቦታ ኢያሱ ሲተካ የተለወጠው ሰው እንጂ እግዚአብሔር ያው እግዚአብሔር ነው:: ለኢያሱ ዮርዳኖስና ኢያሪኮ አዲስ ቢሆኑበትም እግዚአብሔር ግን ባሕርን ከፍሎአል፤ ከአማሌቅ ጋር በነበረው ጦርነት ድል ሰጥቶአል፤ ሕዝቡን እየመገበ መርቷል:: ይህ ያልተለወጠው እግዚአብሔር ኢያሱን «በርታ፤ ጽና» ይለዋል::

ኢያሱ የመሪነቱን ኃላፊነት የወሰደው ለብቻው አልነበረም:: «ከአንተ ጋር ነኝ» (ኢያ 1:9) ያለው እግዚአብሔር አብሮት አለ::

ዛሬም ቢሆን እግዚአብሔር ከመረጣቸውና ፈቃዱን ሊያደርጉ ከሚወስኑ መሪዎች ጋር እርሱ አብሮአቸው እንደሚሆን ይህ ተስፋ


የጸና ነው:: ጌታ ‹አይዞህ› ሲል ቃሉ ጉልበት የሚኖረው ተናጋሪው ከቃሉ ጋር ስለሚሆን ነው:: በክርስቲያናዊ አመራር መሪው ዘወትር መጠየቅ የሚገባው ‹እግዚአብሔር ከእኔ ጋር አለ ወይ?›፤ ‹የቆምሁት ከእግዚአብሔር ወገን ነው ወይ?› በማለት መሆን ይኖርበታል::

## 10.3 ከአጀማመር ይበልጥ ለአጨራረስ መጠንቀቅ

የጌታ ቃል «ሙሉ ደመወዝን እንድትቀበሉ እንጂ የሠራችሁትን እንዳታጠፉ ለራሳችሁ ተጠንቀቁ» (2ዮሐ 8) በማለት ሩጫውን በጽናት ለሚፈጽም ሰው ስለሚጠብቀው ብድራት ይገልጻል:: ጳውሎስም ስለ ደመወዝ ሲናገር «ወደ ፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል፤ ይህንም ጻድቅ ፈራጅ የሆነው ጌታ ያን ቀን ለእኔ ያስረክባል፤ ደግሞም መገለጡን ለሚወዱት ሁሉ እንጂ ለእኔ ብቻ አይደለም» (2ጢሞ 4:8) ብሏል:: እንዲሁም ያዕቆብ «በፈተና የሚጸና ሰው የተባረከ ነው፤ ከተፈተነ በኋላ ለሚወዱት ተስፋ ስለ እርሱ የሰጣቸውን የሕይወትን አክሊል ይቀበላልና» (ያዕ 1:12) ብሏል።







የክርስትና ሕይወት በሯጮች መካከል የሚደረግ የሩጫ እሽቅድድም ሳይሆን እያንዳንዱ የተሰጠውን የራሱን ሩጫ መሮጥ ነው:: በዚህ ሩጫ «አሸናፊ» ተብሎ የሚሰየም አንድ ሯጭ የለም:: አሸናፊው አንድ ነው፤ እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: ሁላችንም በክርስቶስ ኢየሱስ አሸናፊዎች ነን:: ሁላችንም በውድድሩ ሕግ መሠረት ሮጠን አክሊልን እንድንቀበል ተጠርተናል::

እንዲሁም አብሮን ስለሚሮጠው ወንድማችን ማሰብና መጠንቀቅ ከተቻለም በሩጫው ማገዝ ይገባል:: ይህን አለማድረግ «የወንድሜ ጠባቂው እኔ ነኝን?» (ዘፍ 4:9) የሚለውን መድገም ነው:: በሌላ በኩል ሌላው ወንድም በጌታ ፊት የበለጠ ሞገስ ያገኘ መስሎን

«ይህስ እንዴት ይሆናል?» ብንል «...ምን አግዶህ? አንተ ተከተለኝ» (ዮሐ 21፡21-22) እንባላለን፡፡

ስለዚህ ክርስቲያናዊ መሪ ሙሉ ደመወዙን ከኢየሱስ ክርስቶስ ለመቀበል የሚሠራ ሰው ነው፡፡ በእርሻው ላይ ሠራተኞችን ያሰማራ እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው ብድራትን ይከፍላል፡፡ ሙሉ ደመወዝ ለማግኘት እንደ ካሌብ እግዚአብሔርን «ፈጽሞ» መከተል (ኢያ 14፡8-9) እንጂ እንደ ንጉሡ ሳኦል ለተወሰነ ዘመን ብቻ ታይቶ ቀሪውን ክፍል በአመፅ መሄድ አይደለም (1ዜና 10፡13)፡፡ ይህ ፍጻሜን ማበላሸት ነው፡፡

ሩጫን የሚጨርስ ሰው እንደ ጌታ ኢየሱስ ነውርን የሚንቅ፤ መከራን የሚታገሥ ሰው ነው፡፡ በእርሱ ላይ የሚባለውን ክፉ ነገር ወይም ስድብ ንቆ የተሰጠውን አደራ ለመወጣት የሚተጋ ሰው ነው፡፡ ሩጫን ለመጨረስ ሯጩ ሰው ለግሉ የተሰመረለትን መስመር ሳይለቅና የተሰጠውን ርቀት በመጨረስ እንደ ጌታ «ተፈጸመ» (ዮሐ 19፡30) ለማለት መዘጋጀት አለበት፡፡ እውነተኛ ጽናት የመጨረሻውን የመሮጫ መስመር በድል ማለፍ ነው፡፡

ጳውሎስ በሕይወቱ መጨረሻ ላይ «በመሥዋዕት እንደሚደረግ፥ የእኔ ሕይወት ይሠዋልና፥ የምሄድበትም ጊዜ ደርሶአል። መልካሙን ገድል ተጋድዬአለሁ፤ ሩጫውን ጨርሼአለሁ፤ ሃይማኖትን ጠብቄአለሁ» (2ጢሞ 4፡6-7) አለ፡፡

- ተጋድያለሁ - መጨረሽን፤ ማሸነፍን፤ ድልን፡፡
- ጨርሻለሁ - ተፈጸመ ማለት፤ የሚፈለገው ግብ መድረስን
- ጠብቄአለሁ - ለተገለጠው እውነት ታማኝነትን፤ መንከባከብን ያመለክታል፡፡

ጳውሎስ የሮጠው ይህ ሩጫ ‹የመቶ ሜትር› የሚባለው ዓይነት አጭር ሩጫ አይደለም፡፡ ጌታ በደማስቆ መንገድ ከተገናኘው ቀን





ጀምሮ ለ30 ዓመት ያህል የሮጠው ያልተቋረጠ ሩጫ ነው፡፡ በእነዚህ ዓመታት ጳውሎስ በብዙ መከራ ውስጥ አልፎአል (2ቆሮ 11፡22-27)፡፡ በዚህ ዘመን ይህን ዓለም ወደው እንደ ዴማስ ከሩጫው የወጡም ነበሩ (2ጢሞ 4፡10)፡፡

በአጠቃላይ ከክርስቲያናዊ መሪነት ጋር በተያያዘ አንዳንድ ጊዜ መልካም ጅማሬ የታየባቸው ሥራዎችና ፕሮጀክቶች ለምን እንደታሰበው ሳይጠናቀቁ ይቀራሉ? ብሎ መጠየቅ ይጠቅማል፡፡ ሥራዎች ዳር የማይደርሱበት ምክንያት አንዳንድ ጊዜ ጅማሬው የሰው በሆነ ሀሳብና ምኞት ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ሲሆን አብዛኛውን ጊዜ ግን አጨራረስን ካለማሳመር ጋር በሚመጣ ችግር ምክንያት ነው፡፡ ይህም ጌታ ሲናገር «ከእናንተ ግንብ ሊሠራ የሚወድ ለመደምደሚያ የሚበቃ ያለው እንደ ሆነ አስቀድሞ ተቀምጦ ከሳራውን የማይቈጥር ማን ነው? ያለዚያ መሠረቱን ቢመሠርት፤ ሊደመድመውም ቢያቅተው፤ ያዩት ሁሉ። ይህ ሰው ሊሠራ ጀምሮ ሊደመድመው አቃተው ብለው ሊዘብቱበት ይጀምራሉ» (ሉቃ 14፡30) እንዳለው ነው፡፡

አጨራረስን ለማስማር ጽናት አስፈላጊ ነው፡፡ ለመጽናት ደግሞ ኢየሱስን መመልከት ነው፡፡ «...እኛ ደግሞ ሸክምን ሁሉ ቶሎም የሚከበንን ኃጢአት አስወግደን፤ የእምነታችንንም ራስና ፈጻሚውን ኢየሱስን ተመልክተን፤ በፊታችን ያለውን ሩጫ በትዕግሥት እንሩጥ፤ እርሱ ነውርን ንቆ በፊቱም ስላለው ደስታ በመስቀል ታግሦ በእግዚአብሔር ዙፋን ቀኝ ተቀምጦአልና» (ዕብ 12፡1-3)፡፡ ስለዚህ የመጽናት መንገዱ የክርስቶስን ፈለግ መከተል ሲሆን ግቡ ደግሞ ክርስቶስን ለመምሰል ነው፡፡

ለዚህም ነው ጳውሎስ «ራሴ የተጣልሁ እንዳልሆን ሥጋዬን እየጎሰምሁ አስገዛዋለሁ» (1ቆሮ 9፡27) የሚለው፡፡ ጽናት ራስን ለዓላማ ዲሲፕሊን ማድረግን ይጠይቃል፡፡ እንዲሁም ጢሞቴዎስን

በእምነት በመጽናት ራሱንና ሌላውን እንደሚያድን ሲመክረው «ለራስህና ለትምህርትህ ተጠንቀቅ፥ በእነዚህም ጽና፤ ይህን ብታደርግ፥ ራስህንም የሚሰሙህንም ታድናለህና» (1ጢሞ 4:16) በማለት ይመክረዋል::

ጽናት ከመንፈሳዊ መሪዎች የሚጠበቅ ዓይነተኛ ባሕርይ ነው:: መሪዎች በተሰማሩበት መስክ ሁሉ ጽናት እንዲያሳዩ ይጠበቃል:: «እንደ ተሰጠንም ጸጋ ልዩ ልዩ ስጦታ አለን፤ ...አገልግሎት ቢሆን በአገልግሎታችን እንትጋ፤ የሚያስተምርም ቢሆን በማስተማሩ ይትጋ፤ የሚመክርም ቢሆን በመምከሩ ይትጋ፤ ...የሚገዛ በትጋት ይግዛ» (ሮሜ 12:6-8) እንደሚል:: ስለዚህ የመሪነትን ጸጋ መቀበል አንድ ነገር ሆኖ በተሰጠው ጸጋ በትጋት ማገልገልና እስከ ፍጻሜ በታማኝነት መጽናት ሌላ ነው::

በዚህ ምዕራፍ በስፋት ለማየት እንደሞከርነው በመሪነት ሕንጻ መገንባት «መሠረት» በሆነው ላይ የሚገነቡት አሥሩ ዓምዶች ሁሉም እጅግ አስፈላጊዎች ናቸው:: የተሟላ መሪነት የሚኖረው እያንዳንዳቸው በነጠላ እንዲሁም ሁሉም በአንድነት በክርስቲያናዊ መሪ ሕይወት ሲታዩ (ሲገኙ) ነው::

የጀመርነውን የሕንጻ ግንባታ በመቀጠል እነዚህ ሁሉ ዓምዶች እንዴት እንደሚያያዙና የሕንጻው ድምድማት ምን እንደሚሆን በሚቀጥለው ምዕራፍ እንመለከታለን::






## ክፍል ሦስት

# የክርስቲያናዊ መሪነት ሕንጻ ድምድማት፡- ፍቅር

በዚህ መጽሐፍ መሥራት ለጀመርነው የክርስቲያናዊ መሪነት ሕንጻ ሁሉን የሚያያይዘው ድምድማቱ ፍቅር ነው:: የሁሉ ማሰሪያ ፍቅር ነው:: የሕግም ፍጻሜ ፍቅር ነው:: የክርስቲያናዊ መሪም እውነተኛ መንፈሳዊነት መለኪያው የፍቅርና የአንድነት ምሳሌ መሆኑ ነው::

እረኝነት የሚለው ቃል ሲነሣ ቀድሞ የሚመጣው ሃሳብ ፍቅርና ከፍቅር የተነሣ የሚለው ነው:: ይህን በተለያየ መልኩ ቀጥለን እንመለከታለን:: እረኝነትን- «መልካም እረኝነት» የሚያደርገው ፍቅር ነው::



## 3.1 የእረኝነት ማሰሪያ ድምድማቱ የመንጋውን ባለቤት መውደድ ነው፡፡

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለጴጥሮስ አገልግሎትን ሲሰጠው ሦስት ጊዜ የካደውን ሦስት ጊዜ ደጋግሞ «ከእነዚህ ይልቅ ትወደኛለህን?» ብሎ ጠየቀው፡፡ ጴጥሮስ ጌታን እንደሚወደው ሲመልስለት «...አሰማራ ...ጠብቅ ...አሰማራ»[42] (ዮሐ 21፡15-17) አለው፡፡

ጌታ ለጴጥሮስ አደራ ከመስጠቱ አስቀድሞ «ትወደኛለህን?»[43] በማለት በተደጋጋሚ መጠየቁ የሚያስገነዝበን ትልቅ ቁም ነገር አለ፡፡ ከጌታ አደራ የሚቀበል ወይም ኃላፊነት የሚሰጠው ሰው ከሚጠበቅበት መስፈርት የመጀመሪያው ኃላፊነትን የሚሰጠውን ጌታ መውደዱ ነው፡፡ እረኝነት ጌታ ኢየሱስን ከማንም (ከምንም) ይልቅ አብልጦ ከመውደድ የተነሣ የሚደረግ አገልግሎት ነው፡፡ ክርስቲያናዊ መሪነት ለአገልግሎት የጠራውን ጌታ ከመውደድ ይጀምራል፡፡

እዚሁ ዮሐ 21፡15-17 ባለው ክፍል «ትወደኛለህን?» ስለሚለው ቃል አገባብ ጥቂት እንይ፡፡

ጌታ ኢየሱስ ጴጥሮስን «ትወደኛለህን?» ብሎ ሦስት ጊዜ ሲጠይቀው በቁጥር 15ና 16 የተጠቀመው ‹አጋፔ› የሚለውን የግሪክ ቃል ሲሆን በቁጥር 17 ደግሞ ‹ፊልዮ› የሚለውን የግሪክ ቃል ነው፡፡ በአንጻሩ ጴጥሮስ ኢየሱስን እንደሚወደው ሦስት ጊዜም የመለሰለት ‹ፊልዮ›

---

[42] The word used in Joh 21:15, Joh_21:17, is *boske*, which strictly signifies to *give them food;* but the word used in Joh_21:16 is *poimaine*, which signifies more largely to do all the offices of a shepherd to them:

[43] Love ([agapas](G0025)).





የሚለውን ቃል በመጠቀም ነበር፡፡ የግሪኩ ቃል አጋፔ ‹ራስን የመስጠት ፍቅርን› ሲያመለክት ፊልዮ ደግሞ ‹እንደ ወንድም ማፍቀርን› ያመለክታል፡፡

ቁ.15 ኢየሱስ - ትወደኛለህን (አጋፔ)[44]? - ራስን በመስጠት ዓይነት ፍቅር ትወደኛለህን?

ጴጥሮስ - እንድወድህ (ፊልዮ)[45] አንተ ታውቃለህ - እንደ ወንድም በሆነ መውደድ/ ማፍቀር

ቁ.16 ኢየሱስ - ትወደኛለህን (አጋፔ)? - ራስን በመስጠት ዓይነት ፍቅር ትወደኛለህን?

ጴጥሮስ- እንድወድህ (ፊልዮ) አንተ ታውቃለህ - እንደ ወንድም በሆነ መውደድ/ ማፍቀር

ቁ.17 ኢየሱስ - ትወደኛለህን (ፊልዮ)[46]? - እንደ ወንድም ታፈቅረኛለህን?

---

[44] Agapás - GK. agape (ag-ah'-pay); from NT:25; love, i.e. affection or benevolence; NT:26 agapao (ag-ap-ah'-o); to love (in a social or moral sense). KJV - (dearly, well) beloved, dear.

[45] Filoó- NT:5368 phileo (fil-eh'-o); from NT:5384; to be a friend to (fond of [an individual or an object]), i.e. have affection for (denoting personal attachment, as a matter of sentiment or feeling;
Agape (NT:250 is wider than Filoo (NT:5368), embracing especially the judgment and the deliberate assent of the will as a matter of principle, duty and propriety: the two thus stand related very much. (Biblesoft's New Exhaustive Strong's Numbers and Concordance with Expanded Greek-Hebrew Dictionary. Copyright © 1994, 2003, 2006 Biblesoft, Inc. and International Bible Translators, Inc.)

[46] fileís

ጴጥሮስ - እንድወድህ (ፊልዮ) አንተ ታውቃለህ - እንደ ወንድም እንደማፈቅርህ አንተ ታውቃለህ

ጌታ ኢየሱስ በሦስተኛው ጥያቄው አጋጼ ከሚለው ቃል ፊልዮ ወደሚለው በመለወጡ ላይ ብዙ ማለት አይቻለንም፡፡ ሁለት ጊዜ አጋጼን ተጠቅሞ በሦስተኛው ፊልዮን መጠቀሙ ምናልባት ጴጥሮስ ራሱን አሳልፎ በመስጠት ያህል ፍቅር ኢየሱስን ለመውደድ ቢቸገር እንኳን ‹እንደ ወንድም › ይወደው እንደሆነ ሲጠይቀው ይመስላል። እዚህ ላይ እኛ መገንዘብ ያለብን ዋና ነገር ከጌታ ኢየሱስ የአገልግሎት አደራን የሚቀበል ሰው አስቀድሞ ክርስቶስን መውደድ እንደሚጠበቅበት ነው፡፡ ጴጥሮስ የበጎች እረኛ ለመሆን አስቀድሞ የበጎችን ባለቤት ኢየሱስን መውደድ ይገባው ነበር፡፡

እግዚአብሔርን የሚወድ ሰው የእግዚአብሔር የሆኑትን ሕዝቡን (መንጋውን) ይወዳል (1ዮሐ 5፡1-2)፡፡ ታላቁ እረኛ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መንጋውን ሁልጊዜ ይወድዳል፡፡ ራሱን የሰጠው ስለ በጎቹ ነውና በጎቹን (ዮሐ 10፡14፤27) እርሱን ለማይወድ ሰው አሳልፎ አይሰጥም፡፡

ሐዋርያው ጳውሎስም ስለ አገልግሎቱ ሲናገር «የክርስቶስ ፍቅር ግድ ይለናልና» (2ቆሮ 5፡14) ይላል፡፡ ስለዚህ ክርስቲያናዊ መሪ የሚያገለግለውን መንጋ የሚወደው ራሱ በክርስቶስ ፍቅር ውስጥ ሆኖ ነው፡፡

«ከእነዚህ ይልቅ» የሚለውን የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪዎች የተለያየ ትርጉም ይሰጡታል፡፡ ጴጥሮስ አሣ አጥማጅ ነበርና ኑሮውን ከመሰረተባቸው ዕቃዎችና ንብረቶች፡- ከጀልባዎቹ፤ ከአሦቹና ከመረቦቹ ይልቅ ማለት እንደሚሆን የሚገምቱ አሉ፡፡ ሆኖም «ከእነዚህ ይልቅ» ለሚለው የተሻለ መረዳት የሚሆነው «ከእነዚህ ደቀ መዛሙርት ይልቅ» የሚለው ነው፡፡ ምክንያቱም ጌታ አልፎ በተሰጠባት ሌሊት ጴጥሮስ «ሁሉም በአንተ ቢሰናከሉ እኔ





ከቶ አልሰናከልም» (ማቴ 26፡33፤ ማር 14፡29) በማለት ከሌሎች ደቀ መዛሙርት አንጻር ራሱን ለጌታ ታማኝ አድርጎ ገልጦ ነበር፡፡ አሁን እዚህ ላይ ጌታ «ከእነዚህ ይልቅ» ሲለው ከቅርብ ጓደኞቹ (ከዮሐንስና ከያዕቆብ፤ ወይም ከገዛ ወንድሙ ከእንድርያስ) አስበልጦ ጌታን ይወድ እንደሆነ መጠየቁ ሊሆን ይችላል፡፡

ቀደም ሲል በዮሐ 21፡15-17 እንዳየነው ጌታ ኢየሱስ ጴጥሮስን ያዘዘው በጎችን እንዲጠብቅ ነው፡፡ ጴጥሮስም በመልእክቱ ለሚጽፍላቸው ሽማግሌዎች የእግዚአብሔርን መንጋ በፍቅር እንዲጠብቁ ይነግራቸዋል (1ጴጥ 5፡1-4)፡፡ በዚህ ክፍል ስለ እረኝነት አገልግሎት በርካታ ነጥቦችን እናገኛለን፡፡

ሀ. ተግባሮች

የእረኝነት ተግባር የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡፡

- መጠበቅ[47] (5፡2)፡፡
- መመገብ - ምግብና ውኃ መስጠት፤ በጸጉራቸው ውስጥ ከሚገቡ እሾህና ተባዮች ጤንነታቸውን መንከባከብ
- መምራት - ዕረፍት ወደሚያደርጉበት፤ ከአራዊት ሳይሰጉ ወደሚመሰጉበት መምራት፤
- ማሰማራት - ከሚሰርቁ ሌቦች፤ ከአደጋ፤ በጎቹን ከሚተናኮሉ አራዊት ሁሉ መጠበቅ
- መንብኘት (5፡2)- በፍቅርና በንጹህ ልብ ማስተዳደር (ከመንጋው ተነጥለው የሚኮበልሉ በጎችን መጠባበቅ፤ ከሄዱም ፈልጎ መመለስ)
- ምሳሌነት[48] (5፡3) – ሌሎች በመልካም የሚመለከቱት አርአያነት

[47] "tend," verb denotes all that is included in the office of a shepherd -- guiding, guarding, folding,

### ለ. የተግባሮች አፈጻጸም

እነዚህ ተግባሮች የሚከናወኑት

- በግድ ሳይሆን በውድ
- መጥፎን ረብ (ጥቅም) በመመኘት ሳይሆን በበጎ ፈቃድ፤
- በኃይል በመግዛት[49] ሳይሆን በምሳሌነት

መጥፎውን ረብ የሚፈልጉ ዋጋቸውን በምድር ለመቀበል የቆረጡ ናቸው:: በበጎ ፈቃድ (በመውደድና በፍቅር) የሚያገለግሉ ደግሞ የማያልፈውን የክብር አክሊል የእነርሱና የሁሉም እረኞች አለቃ ከሆነው ከኢየሱስ ክርስቶስ ለመቀበል የተዘጋጁ ናቸው::

### ሐ. «የእረኞች አለቃ» ኢየሱስ ክርስቶስ:-

- የበጎቹ ባለቤት ነው:- ሁሉም በጎች የእርሱ ናቸው:: እርሱ በደሙ ገዛቸው፤ እርሱ በሁሉም ላይ ገዥ ነው:: ከክፉ ሁሉ ይጠብቃቸዋል::
- የእረኞች አለቃ ነው:- በሁሉም እረኞች ላይ አንድ አለቃ እረኛ አለ፤ እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: ሌሎች እረኞች ሁሉ የእረኝነት ሥልጣንን ከእርሱ ይቀበላሉ፤ በስሙ ሥልጣን ያገለግላሉ፤ ለእርሱም ተጠያቂዎች ናቸው::

[48] ምሳሌ የሚለው በ1ጴጥ 2:21 «ክርስቶስ ደግሞ ፍለጋውን እንድንከተል ምሳሌ ትቶላችሁ» ሲል የጽሑፍ ግልባጭ ዓይነት የሚል ፍቺ አለው:: [hupogrammos] (G5261), "a writing-copy" (1 Pet. 2:21); በ2ጴጥ 2:6 «ኃጢአትንም ያደርጉ ዘንድ ላሉት ምሳሌ አድርጎ» ሲል ለሕንጻ ሥራ ዲዛይኑ ምሳሌው እንደሆነ ዓይነት ነው:: [paradeigma](G3856), "an architect's plan or a sculptor's or painter's model" (2Pet. 2:6);

[49] በኃይል አትግዙ:- As lording it ([katakurieuontes](G2634)). ሌላውን ማስጨነቅ/ መግዛት በማቴ 20:25 እንደተገለጸው ዓይነት::





- ዋጋን ይከፍላል:- አገልግሎታቸውን ለጊዜያዊ ጥቅም ሳይሆን በበጎ ፈቃድ ለፈጸሙት የማያልፍ የክብር አክሊል ይሰጣቸዋል:: የዘላለም ዋጋን መክፈል ሥልጣን ያለው እርሱ ብቻ ነው::

ጥበበኛ ገበሬ በእርሻው ውስጥ ያለ እያንዳንዱ ተክል በመስኖ ውኃ እንዲደርሰው እንደሚያደርግ ሁሉ መልካም እረኛም በመንጋው ውስጥ ለእያንዳንዱ በግ ይጠነቀቃል:: መንጋው የእያንዳንዱ ጤናማ በግ ድምር ውጤት ነው::

## 3.2 የክርስቲያን መሪዎች ዋና ትኩረት የእግዚአብሔር ሕዝብ ነው::

«የእግዚአብሔር እድል ፈንታ ሕዝቡ ነው» (ዘዳ 32:9):: እግዚአብሔር «የእኔ» የሚለው ትልቁ ሀብት፤ «እንደ ዓይን ብሌን» የሚያየው እርሱ የታደገውንና ያዳነውን ሕዝቡን ነው:: የዚህ የከበረና «ታላቅ» ሕዝብ አገልጋይ ሆኖ በእግዚአብሔር መመረጥ በምድር ላይ ከሚገኝ ሥራ ሁሉ የላቀ ነው::

የእረኝነትን ቦታ ለደመወዝ የሚፈልገው በከንቱ ተመኘው:: ለእንጀራው የሚሠራ ሰው «መብል ለሆድ ነው፤ ሆድም ለመብል ነው፤ እግዚአብሔር ግን ይህንም ያንም ያጠፋቸዋል» (1ቆሮ 6:13) እንደ ተባለ አላስተዋለምን? ስለዚህ ክብር በሌለበት፤ ሰማያዊ መታሰቢያ በሌለው ሥራ ደከመ:: በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ አለቃ እንዲሆን የሚሾም ሰው እግዚአብሔር ያከበረውንና የሚወደውን ሕዝብ ካልወደደ በስተቀር መሪ ሊሆን አይገባውም::

መሪ ከሁሉም በላይ ስለ ሰዎች ነፍስ ይጠየቃል (ዕብ 13:7):: በክርስቶስ ወንበር ፊት ተጠያቂ ሆኖ ይቀርባል:: በእግዚአብሔር ፊት ሂሳብ ያወራርዳል:: ስለዚህ እረኞች ለሚጠብቋቸው በጎች

ስለሚመገቡት፤ ስለሚውሉበት ሥፍራ፤ ስለ እድገታቸው እና ስለ ጥበቃቸው ኃላፊነት አለባቸው::

መልካም እረኛ ያለው ሕዝብ የሚያሰማራውና የሚጠብቀው አለው፤ የሚበላውም ያገኛል:: እረኛ የሌለው ወይም እረኛው ምንደኛ በሆነበት ሁኔታ በጎቹ ረዳት የሌላቸው፤ የኮሰመኑ፤ የተረሱ ይሆናሉ:: እንዲህ ዓይነት እረኛ ለበጎች ርኅራኄ የለውም::

መልካሙ እረኛ ጌታ ኢየሱስ «ብዙ ሕዝብም ባየ ጊዜ እረኛ እንደሌላቸው በጎች ተጨንቀው ተጥለውም ነበርና አዘነላቸው» (ማቴ 9:36):: መልካም እረኝነት ለሌላው መጠንቀቅ፤ መመገብ፤ ማሰማራት ነው::

የሰውን ልብ ሁሉ የሚመዝነው ጻድቅ እግዚአብሔር ሰዎች ወደ አገልግሎት የሚገቡበትን ዓላማ ያውቀዋል:: የእግዚአብሔር አገልግሎት ለደመወዝተኝነት፣ የማዕረግ መጠሪያ ለማግኘት፣ ለክብሬታ ወይም ለጥቅም፣ የሚፈልጉት ሥራ አይደለም:: የእግዚአብሔርን ሥራ ለመሥራት መወሰን ክርስቶስን ከመውደድ የተነሣ የፍቅርና የመሰጠት መግለጫ ነው:: ስለዚህ አገልግሎትን በተመለከተ ዋናው ቁም ነገር ምን ትሠራለህ? ሳይሆን ለምን ትሠራዋለህ? ነው::

## 3.3 «ፍቅር ግን ከሌለኝ ከንቱ ነኝ»

ያለ ፍቅር የተደረገ የጸጋ ስጦታን መግለጥ፣ መልካም ሥራ ማድረግ ወይም ታላቅ መከራን መቀበል ሁሉ ከንቱ[50] ነው:: በሰማይ ብድራት የማይጠብቀው ምድራዊ ድካም መሆኑ ነው::

[50] ከንቱ የሚለው ቃል ባዶ ወይም ዜሮ የሚል ፍቺ አለው::





የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን መልአክ[51] ሥራ የበዛለት ሥራውንም በትዕግሥትና በትጋት የሚሠራ ነበር (ራእ 2:1-7):: ሌላም ብዙ መልካም ሊባሉ የሚችሉ ሥራዎች ነበሩት:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አገልግሎት የበዛላቸው «የሥራ መሪዎች» ሆነው ነበር:: ትኩረታቸው በሥራው ላይ እንጂ በኅብረት ላይ አልነበረም:: ከአገልግሎት ሁሉ ቀዳሚውን ነገር ማለትም ፍቅርን ትተዋል:: በሥራ መትጋታቸው ቢያስመሰግናቸውም ትልቅ ነገር ጎድሏቸዋል:: በእግዚአብሔር ሚዛን መቅረዙ ሊወሰድበት የተቃረበ ሆኗል:: ምክንያቱም የሚሠራውን ሁሉ ያለ ፍቅር ስለሚሠራ፣ የመጀመሪያውን ፍቅር ስለ ተወ::

በመሪነት ላይ ያሉ ሰዎች ምናልባትም ልብ ሳይሉት በሥራ ይዋጡና የሥራውን ባለቤት ይረሱታል:: ፍቅራቸው ከሥራው ጋር ሆኖ መወደድ የሚገባው ሥራውን የሰጠው እግዚአብሔር መሆኑን ይዘነጉታል:: ከዚህም የተነሣ ምንም እንኳን «ጥሩ» የሚባል ተግባር ቢያከናውኑም በፍቅር አላደረጉትምና በእግዚአብሔር ፊት ሞገስ አይኖራቸውም::

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚደረጉ አገልግሎቶች ለክርስቶስ ካለው ፍቅር የተነሣ ካልተደረጉ በስተቀር «ሃይማኖታውያን ተግባሮች/ ሃይማኖታውያን ግዴታዎች» ብቻ ይሆናሉ:: ነፍስ የሌለው ሥጋ እንደ ማለት ነው:: በኤፌሶን ቤተ ክርስቲያንም አገልግሎቱና ተጋድሎው እንደ ሃይማኖት ግዴታ እንጂ ለክርስቶስ ካላቸው ፍቅር የተነሣ ባለመሆኑ ነበር::

በ1ቆሮ 13:1-3 የተዘረዘሩት የከበሩ የጸጋ ስጦታዎች፤ አገልግሎቶችና መልካም ሥራዎች ሆነው ሳሉ ያለ ፍቅር የተደረጉ ከሆነ ከንቱ ወይም ባዶ መሆናቸውን ያስረዳል:: እነዚህም:- በልሳን መናገር፣

[51] መልአክ-ተኛ-መሪ:: GK: aggelos (ang'-el-os); from aggello a messenger; especially an "angel"; by implication, a pastor, leader

ትንቢት መናገር፣ ምሥጢርንም ሁሉ እውቀትን ሁሉ ማወቅ፣ ተራሮችን የሚያፈርስ እምነት፣ ያለውን ሁሉ ለድሆች ማካፈል፣ ሥጋን ለእሳት መቃጠል አሳልፎ መስጠት:: እነዚህ ልሳን፣ ትንቢት፣ እምነትና መስጠት ከመንፈስ ቅዱስ የሚሰጡና እጅግ የከበሩ ጸጋዎችና ዋጋ የሚያስከፍሉ አገልግሎቶች ሆነው ሳለ ያለ ፍቅር የተነገረ ልሳንና ትንቢት ንግግሩም ጩኸትና መንሸዋሸዋት ብቻ ይሆናል:: እንዲሁም ራስን መሥዋዕት አድርጎ በማቅረብ ከፍተኛ ዋጋ የተከፈለበትም አገልግሎት ቢሆን ያለ ፍቅር ከንቱ ይባላል::

## 3.4 እረኞችም ሰዎች ናቸው:- መወደድን ይፈልጋሉ

ሰዎች ሁሉ ሁልጊዜ አንድ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ላይሆኑ ይችላሉ:: አንዳንዶቹ በደስታና በምስጋና ሌሎቹ ደግሞ በሃዘንና በትካዜ በተለያየ ስሜት ውስጥ ይሆናሉ:: ከመሪ አገልግሎት አንዱ የሚመራቸው ሰዎች በተለይም ደግሞ በቅርቡ ላሉት የቡድኑ አባላት ያሉበትን ሁኔታ የመረዳትና በሁኔታቸው ጠጋ ብሎ ማጽናናት፤ መደገፍ፤ አብሮአቸው መደሰት፤ አብሮም ማልቀስ ጭምር ነው:: እግዚአብሔር ሕዝቡን የሚመክር፤ የሚያስተምርና የሚገስጽ ነው:: ደግሞም እግዚአብሔር ሕዝቡን የሚያጽናና፤ ተስፋ የሚሰጥና የሚደግፍ ነው::

እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ የተቆጣበት ጊዜ ነበር:: ደግሞም የሚጽናናበት ጊዜ እንደ መጣና ከእግዚአብሔር መጽናናት እንደሆነለትም ሲናገር «አጽናኑ ሕዝቤን አጽናኑ ይላል» (ኢሳ 40፡1)::

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ በዮሐ 13 የሚሄድበት ጊዜ እንደ ደረሰ ከነገራቸው በኋላ በ14፡1 ላይ «ልባችሁ አይታወክ፤ በእግዚአብሔር እመኑ፤ በእኔም ደግሞ እመኑ» ይላቸዋል:: ከእርሱ





መሄድ ጋር ሀዘን፤ ትካዜና የልብ መታወክ በደቀ መዛሙርቱ ላይ ይመጣል:: መሄዱ እውነትና የማይቀር ቢሆንም እነርሱ ግን እንዳያዝኑ ያጽናናቸዋል::

የሕዝብ አለቆች ምንም ያህል «ትልልቅ አገልጋዮች» ቢሆኑም ራሳቸውም ሰዎች ናቸው:: እነርሱም «በተራቸው» የሚያዝኑበት ሁኔታ ይመጣል፤ የሰውን ፍቅርና እንክብካቤ ይፈልጋሉ:: የሚያገለግሏቸውም ሕዝብ እንደሚቀበላቸውና እንደሚወዷቸው እርግጠኛ መሆን ይሻሉ::

ኤልያስ ታላቅ የእግዚአብሔር ነቢይ ነበር:: በአምላኩ የታመነ ታላቅ የእግዚአብሔር ሰውና ከ450 የበዓል ነቢያት ጋር ተወዳድሮ ድል ያደረገ ነበር (1ነገ 18):: መንፈሳዊ ሥራ በሰው ብዛት ሳይሆን ከእግዚአብሔር ወገን በመሆን እንደሚከናወን የተረዳው ኤልያስ ከበዓል 450 ነቢያት ጋር ብቻውን የተገዳደረና (18፡22) እርሱ የሚያመልከው አምላክ ሕያው መሆኑን ያሳየ ነቢይ ነበር (18፡16):: ኤልዛቤል በዛተችበት ጊዜ «ኤልያስም ፈርቶ ተነሣ» (19፡3) ተብሏል:: «እግዚአብሔርንም ይበቃኛል አሁንም አቤቱ እኔ ከአባቶቼ አልበልጥምና ነፍሴን ውሰድ ብሎ እንዲሞት ለመነ» (19፡4)::

በእግዚአብሔር ኃይል ያገለገለ ይህ ታላቅ ነቢይ ገና ያልከበረ ሥጋ አለውና ከዛቻው የተነሣ ፈራ ወደ እግዚአብሔርም ጮኸ:: በዚህ ሁኔታ ኤልያስ የሚያስፈልገው የሚያበረታውና የሚደግፈው ነው:: ስለሆነም በዚህ ጊዜ «መልአክ ዳሰሰው፤ ተነስተህም ብላ አለው» (19፡5) እንዲሁም «ሁለተኛ ጊዜ መጥቶ ዳሰሰው» (19፡7):: እንዲህ ለፈራና መሞትን ለሚመኝ ሰው በዚህ ጊዜ የሚያስፈልገው እውነትን መናገር ብቻ ሳይሆን መዳሰስም ነው:: በመዳሰስ የተወደደ ሰው እንደሆነ ማሳየት ነው:: ዳሰሰው ተነስቶም እንዲበላ ነገረው፤ ገና ብዙ መንገድ እንዳለው ነገረው፤ ተነስ አለው:: ከዚያ

በኋላ «እስከ እግዚአብሔር ተራራ እስከ ኮሬብ ድረስ ሄደ» (19:8)፡፡

«ኤልያስ እንደ እኛ ሰው ነበረ» (ያዕ 5:17) ተብሎ እንደ ተጻፈ ሁሉ መሪዎችም ሰዎች ናቸው፡፡ ታላላቅ የሚባሉ መሪዎችም ሰዎች ናቸው፡፡

መንገዱን ገና ያልጨረሰ አንድ ታላቅ የእግዚአብሔር ሰው መንገዱን ሳይጨርስ ሞትን የሚፈልግበት ሁኔታ ሊመጣ ይችላል፡፡ ታላላቅ መሪዎች በእግዚአብሔር ኃይል ድንቅና ተአምራትን ካዩና በታላቅ የመንፈስ ቅዱስ ምሪት ካገለገሉ በኋላ ለብቻቸው ሲሆኑ የሚሰማቸው «የትንሽነት» ስሜት ሊኖር ይችላል፡፡ በመድረክ እንደታዩትና እንዳገለገሉት ሳይሆን ያልከበረ ሥጋ አላቸውና የራሳቸውን ማንነት ዓይተው ሊያዝኑና ሊተክዙ ይችላሉ፡፡ መልአኩ እንዳደረገው እነዚህ ሰዎች ወዳሉበት ቦታ ሄዶ መዳሰስ፤ ተነሱ ማለት፤ የሚበሉትንና የሚጠጡትን ማቅረብ፤ ገና መንገድ እንደቀረላቸው ማሳየት፤ እንዲሁም ወደ እግዚአብሔር እንዲቀርቡ መደገፍ ትልቅ አገልግሎት ነው፡፡

ሰዎችን የሚያጽናኑ አገልጋዮች ዮናታን ለዳዊት እንዳደረገው ነው፡፡ በሞትና በታላቅ የእግዚአብሔር ሰዎች መካከል አንድ እርምጃ ብቻ በቀረበት ሁኔታ ውስጥ መጥተው ሰዎቹ እንዳይሞቱ ከፋም እንዳይደርስባቸው የሚያጽናኑ ናቸው (1ሳሙ 20:1-5)፡፡ ለታላቅ የመሪነት አገልግሎት በእግዚአብሔር የተጠሩ ሰዎች ባጭር እንዳይቀሩ ወይም እንዳይሰነካከሉ የሚጠነቀቁና ወደ ሰውም የሚያቀርቡ ናቸው፡፡ በርናባስ ሳውል የተባለውን ጳውሎስን ወደ ሐዋርያት እንዳቀረበው (ሐዋ 9:27)፡፡ እነዚህን በሰው ደረጃ «የእረኞች እረኛ» እንበላቸው!!





ሰውን በእርግጥ የሚያጽናና የመጽናናት አምላክ የሆነው እግዚአብሔር ነው፡፡ እግዚአብሔር ሰውን ሲያጽናና መከራውን ይረሳል፡፡ በፊቱ ያለውን ችግር ሳይሆን የእግዚአብሔርን ታላቅነት ያያል፤ ይደፋፈራል፤ በውስጡ ይጠነክራል፡፡ እግዚአብሔር ሰውን ሲያጽናና ሰው ተስፋ በቆረጠበት፤ በጨለማና በኀዘን ውስጥ ባለበት ጊዜ እግዚአብሔር ወደ ሰው መጥቶ ኀዘኑን ወደ ደስታ ይቀይራል፡፡ በሌሊት መዝሙርን ይሰጣል (ኢዮ 35:10)፡፡ ካለበት የትካዜ ጉድጓድ ውስጥ ያወጣዋል፡፡ ስለዚህ ሰዎች ካሉበት ኀዘን ውስጥ ወጥተው እንዲጽናኑና ሐሴት እንዲያደርጉ ለሰዎች መጸለይና ከሰዎቹም ጋር አብሮ መጸለይ ያስፈልጋል፡፡ ስለሆነም አንዱ የመደገፊያና የማጽናኛ መንገድ የመጽናናት አምላክ መጽናናቱን እንዲልክ ከሰዎቹ ጋር አብሮ መጸለይ ነው፡፡ ስለዚህ ለመሪዎች የሚጸልዩ ሰዎች ትልቅ አገልግሎት እየፈጸሙ ነው፡፡

## 3.5 እውነትን በፍቅር

በሌላ በኩል ደግሞ መሪ የሚመከር፤ የሚደገፍና የሚያጽናና ብቻ አይደለም፡፡ መሪ የሚገሰጽና የሚያስጠነቅቅም ጭምር ነው፡፡ ጌታ ኢየሱስ ሲያስተምር፡- «ለራሳችሁ ተጠንቀቁ፤ ወንድምህ ቢበድልህ ገስጸው ቢጸጸትም ይቅር በለው» (ሉቃ 17:3) እንዳለው፡፡ መሪ መካሪ ብቻ አይደለም፡፡ ራሱም ሰው ነውና በሚገሰጽበት ሁኔታ ውስጥ ሆኖ ከተገኘ በአግባቡ ሊገሰጽ ይገባዋል፡፡

ሐዋርያው ጳውሎስ ሐዋርያው ጴጥሮስን ገስጾት ነበር፡፡ «ፊት ለፊት ተቃወምሁት ይፈረድበት ዘንድ ይገባ ነበርና» (ገላ 2:11) አለ፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ሲመክረው፡- «ቃሉን ስበክ፤ በጊዜውም አለ ጊዜውም ጽና፤ ፈጽመህ እየታገስክና እያስተማርክ ዝለፍና ገስጽ፤ ምክርም» (2ጢሞ 4:2)[52] ብሎታል፡፡ ለቲቶ

[52] በአዲሱ መደበኛ ትርጉም «ቃሉን ስበክ፤ ጊዜው ቢመችም ባይመችም ዝግጁ ሁን፤ በታላቅ ትዕግሥትና በማስተማር አቅና ገስጽ አበረታታ፡፡»

በላከለትም መልእክት «የአይሁድን ተረትና ከእውነት ፈቀቅ የሚሉትን ሰዎች ትእዛዝ ሳያዳምጡ በሃይማኖት ጤናሞች እንዲሆኑ በብርቱ ዉቀሳቸው» ብሎ ይመክረዋል (ቲቶ 1:13)::[53]

የመሪ አንዱ ኃላፊነት ሊገሰጽ የሚገባውን በመገሰጽ ማቅናትና ማስተካከል ነው:: እንዲሁም የደከመውን ማበረታታት ነው:: ምክርና ተግሳጽን የሚሰማ ሰው እንደ ዳዊት ከኃጢአቱ ይመለሳል፤ የእግዚአብሔርንም ምሕረት ያገኛል፤ እግዚአብሔርም ወደ አሰበለት ትልቅ የአገልግሎት ደረጃ ያድጋል:: ዳዊት የነቢዩ ናታንን ተግሳጽ ሰምቶ ንስሐ የገባ ሰው ነው (2ሳሙ 12:13)፡፡ ስለሆነም አጥብቆ መገሰጽ ወይም በብርቱ መውቀስ የሚያስፈልግበት ጊዜ እንዳለ ማስተዋል ይገባል::

እንግዲህ መሪዎች የሚመከሩ፤ የሚያጽናኑ፤ የሚዳስሱ፤ የሚያበረታቱ፤ የሚገስጹ በብርቱም የሚወቅሱ ናቸው:: ሁሉም ሰው ተግሳጽና ወቀሳ አያስፈልገውም:: ሁሉም ደግሞ መዳሰስ ወይም መጽናናት ላያስፈልገው ይችላል:: ስለዚህ የትኛውን አገልግሎት ለማን፤ መቼ፤ በምን ሁኔታ ውስጥ፤ ለመስጠት እንደሚያስፈልገው አውቆ ያንን አገልግሎት ለመፈጸም ትልቅ ጥበብ ያስፈልጋል:: ጥበብ ደግሞ የጥበብ ሁሉ ባለቤት ከሆነው ከእግዚአብሔር ዘንድ ይገኛል::

በእውነት ላይ ተመርኩዞ መገሰጽ፤ መምከርና መውቀስ ተገቢ ሲሆን ይህን ለማድረግ ሁልጊዜም ቢሆን «እውነትን በፍቅር» (ኤፌ 4:15) በሚለው የእግዚአብሔር ቃል መመሪያ መሠረት መሆን ይገባዋል:: የሚገሰጸውም ሰው ኃይለኛ ሰይፍ የሚወድቅበት ከፍቅር የተነሣ

[53] በአዲሱ መደበኛ ትርጉም «አጥብቀህ ገስጻቸው ይኸውም ትክክለኛ እምነት እንዲኖራቸውና ተረት ወይም ከእውነት የራቁትን ሰዎች ትእዛዝ እንዳያደምጡ ነው::»





እርሱን ለማቅናት እንደሆነ ሊገነዘብ ያስፈልገዋል:: ያለበለዚያ የሚወቀሰውና የሚገሰጸው ሰው ከመቃናት ይልቅ የበለጠ ሊጎዳና «ሊሰበር» ይችላል::

የሚወቀሰውም ሰው ወቀሳንና ምክርን ለመስማት ጥበበኛ ሰው መሆን አለበት:: «የሕይወትን ተግሳጽ የሚሰማ ጆሮ በጠቢባን መካከል ይኖራል» (ምሳ 15:31) እንደሚል:: ተመካሪው ለመታረምና ለመስተካከል ራሱን የሚያዘጋጅ ካልሆነ ሰነፍ ሰው መሆኑ ነው:: ለሰነፍ ደግሞ ምክርና ተግሳጽ አይጠቅመውም:: መካሪው ምክሩን በፍቅር ማድረግ እንዳለበት ሁሉ የሚመከረውም ምክርን ለመስማት ጠቢብ መሆን ይገባዋል::

ስታመነዝር የተገኘችዋን ሴት እንደ ሕጉ ትወገር ብለው አይሁድ ለጌታ ጥያቄ ባቀረቡለት ጊዜ ጌታ ኢየሱስ «ከእናንተ ኃጢአት የሌለበት አስቀድሞ ይውገራት» (ዮሐ 8:7) አላቸው:: ይህችን ሴት የከሰሷት የሕግ አዋቂዎች የተመለከቱት አንዲት ሴት ሕግ ስትተላለፍ በመገኘቷ ሕግ መጣሱን ነው እንጂ ራሳቸው ሰው መሆናቸውን አላገናዘቡም:: እንዲሁ ሌላውን ሰው የሚመክርና የሚገስጽ መሪ ራሱ ደግሞ ሰው መሆኑንና ድካም ያለበት እንደሆነ መዘንጋት የለበትም:: ከእግዚአብሔር ጸጋ ብዛት በስተቀር እርሱም እንደ ሌሎቹ ተግሳጽ የሚያስፈልገው ደካማ ጎን ያለው ሰው መሆኑን ማወቅ አለበት:: ስለዚህ ሌላውን ሰው ለመምከር ሲነሣ ገና ባልከበረ ሥጋ መሆኑን ባለመርሳት ራሱን ፍጹም አድርጎ ማቅረብ አይገባውም:: እርሱም ቢሆን የእግዚአብሔር ጸጋ የበዛለት ደካማ ሰው ነውና::

ስለሆነም የሚገስጸውና የሚመከረው ሰው እርሱ በእንደዚያ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ሊገባ የማይችል «ልዩ» ሰው እንደሆነ አድርጎ ራሱን ከፍ በማድረግ በትዕቢት ስሜት እንዳያደርገው መጠንቀቅ ያስፈልገዋል:: እኛ እኮ «ሊራራልን የማይችል ሊቀ ካህናት የለንም»

(ዕብ 4፡15)፡፡ ይህ የሚራራልን ሊቀ ካህን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደኛ የተፈተነ ስለሆነ ነው፡፡ ስለዚህ ሌሎችን የሚመክር፤ የሚያጽናናና የሚወቅስ መሪ በርኅራኄና በፍቅር ሊያደርገው ያስፈልጋል፡፡ የእግዚአብሔርም ቃል የሚለው፡- «ሰው በማናቸውም በደል ስንኳ ቢገኝ መንፈሳውያን የሆናችሁ እናንተ እንደዚህ ያለውን ሰው በየውሃት መንፈስ አቅኑት፤ አንተ ደግሞ እንዳትፈተን ራስህን ጠብቅ...» (ገላ 6፡1-5) ነው፡፡

በማጠቃለል፡- በመሪነት አገልግሎት ላይ ያለሁት ለምንድር ነው? ብሎ ለሚጠይቅ አገልጋይ ቀዳሚው መልስ «እግዚአብሔርን ስለምወድ ነው» የሚል ካልሆነ በስተቀር በአገልግሎት ላይ ያለው በተሳሳተ ምክንያት ነው ማለት ነው፡፡ አንድ ሰው በመሪነት ቦታ ያለው ቦታው ስለሚያስገኝው ከበሬታ፤ ስያሜ፤ ገንዘብ ወይም ሌላም ጥቅማ ጥቅም ከሆነ የእረኝነት አገልግሎት ገና አልገባውም፡፡

ክርስቲያናዊ መሪ (የቤተ ክርስቲያን ወይም የክርስቲያናዊ ድርጅት መሪ) ቢሆን የሚመራቸው ሰዎች ራሱንም ጨምሮ የእግዚአብሔር ልጆች የሆኑ ወንድሞቹ ናቸው፡፡ በቤተ ሰብ ውስጥ ፍቅር እንዲኖር ይጠበቃል፡፡ መሪ ይህንን ፍቅር በሕይወቱ የሚገልጽና የቤተሰቡንም ፍቅር በመጠበቅ ምሳሌ የሚሆን ነው፡፡


የሕንጻውን ግንባታ በመቀጠል በር እናብጅለት፡፡ በሩ ሕንጻው የሚሠራበትን ዋና ዓላማ ይገልጻል፡፡ ይህም በር ወንጌል ነው፡፡





## ክፍል አራት

# የክርስቲያናዊ መሪነት ሕንጻ በር፡- ወንጌል




እስካሁን በዚህ ቅጽ የመሪነት ሕንጻ ጽኑ መሠረት የእግዚአብሔር መሪነትና እረኝነት መሆኑን አየን፡፡ የሕንጻውን አሥር ዋና ዓምዶችም ተመለከትን፡፡ እንዲሁም የሚደመደመው በፍቅር መሆኑን ተገነዘብን፡፡ ግንባታውን በመቀጠል ጉልላት ከማበጀታችን በፊት የመሪነት ሕንጻው የሚገነባው ለምን ዓላማ ነው? የሚለውን ጥያቄ እንስተን መመለስ ይገባናል፡፡ አዎ! የክርስቲያናዊ መሪነት ዋና ግብ ምንድን ነው? መሪነት ለምን ዓላማ ነው?

የክርስቲያናዊ መሪነት ዋና ግብ እግዚአብሔርን ማክበር መሆኑን ወደፊት የሕንጻውን ጉልላት ስንሠራ በስፋት እንመለከታለን:: ለአሁኑ ግን መሪ እግዚአብሔርን የሚያከብረው እንዴት ነው? ስንል ሀሳቡን በማገልገል የሚለውን ቀጥተኛ መልስ ስለምናገኝ የክርስቲያናዊ መሪነት ዋና ግብ የእግዚአብሔርን ሀሳብ በማገልግል እርሱን ማክበር መሆኑን እንገነዘባለን፡

ይህ ከሆነ ደግሞ በአዲስ ኪዳን የእግዚአብሔር የተገለጠ ዋና ሀሳብ ምንድን ነው? ብለን ስንጠይቅ መልሱ «ወንጌል» የሚል ይሆናል:: ወንጌል በሁሉም ቦታና እስከ ምድር ዳርቻ፤ ለሁሉም ዘመንና እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ የተሰጠ የእግዚአብሔር የተገለጠ ሀሳብ ነው::

መሪነት ‹ለውጥ› (ትራንስፎርሜሽን) ላይ ያተኮረ ተግባር ሲሆን በምድር ላይ ከምንም ነገር በላይ ታላቅ ለውጥ ሆነ የሚባለው የሰው ሕይወት ሲለወጥ ነው:: ቁሳዊ በሆነ ተልዕኮና ግብ ላይ በማትኮር ብቻ ‹ምድራዊ ለውጥ› የሚያመጣ ከሆነ የመሪነት ጠቀሜታው ጊዜያዊ ነው:: ጌታ ኢየሱስ «ሰው ዓለምን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱንም ቢያጐድል ምን ይጠቅመዋል? ...» (ማር 8:36-37) እንዳለው ‹ዓለምን ማትረፍ› ግቡ ምድራዊ ነው፤ ከዘላለም አንጻር ሲመዘንም ኪሣራ ነው:: ስለዚህ የሰውን ሕይወት ከመለወጥ የበለጠ የመሪነት ተግባር የለም:: ለዋጩ እግዚአብሔር ሲሆን በለውጡ ሥራ የጌታ አገልጋይ መሆን ከፍተኛው የመሪነት ተልእኮ ነው:: ወንጌል የሰውን ሕይወት የሚለውጥ መለኮታዊ ኃይል ነው::

በሰው ሕይወት መለወጥ ላይ ያላተኮረ መሪነት ጌታ ኢየሱስ «ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣው ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም» (ማቴ 4:4) ያለውን ቃል የዘነጋ ይሆናል:: ሰው በሕይወት ለመኖር ለሥጋው ከምድር ፍሬ የሚገኝ እንጀራና ከሰማይ የወረደ የነፍስ ምግብ ያስፈልገዋል:: የመጀመሪያው





ከምድር የሆነ ምድራዊ ነው፤ ሁለተኛው ከሰማይ የሆነ ሰማያዊ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ «መብል ለሆድ ነው፤ ሆድም ለመብል ነው፤ እግዚአብሔር ግን ይህንም ያንም ያጠፋቸዋል» (1ቆሮ 6:13) እንደሚል ሰው ከመብልና ከሆድ በላይ ነው::

ሰው በምድር ላይ እስካለበት ጊዜ ድረስ የነፍሱ መቀመጫ የሆነው ሥጋው በሕይወት እንዲቆይ እንጀራ አስፈላጊ ነው:: ይሁን እንጂ እንጀራ የዘላለም ሕይወት አይሰጥም፤ እንጀራ የነፍስ ምግብ አይሆንም:: ጌታ «ከሰማይ የወረደ ሕያው እንጀራ እኔ ነኝ፤ ሰው ከዚህ እንጀራ ቢበላ ለዘላለም ይኖራል፤ ...» (ዮሐ 6:51) እንዳለ ይህን ከሰማይ የመጣውን እንጀራ የበላ የዘላለም ሕይወት አለው:: እውነተኛ የሰው ለውጥ (ትራንስፎርሜሽን) ማለትም ይኸው ነው:: ይህ አቻ የማይገኝለት ለዘላለም መለወጥ ነው::

እንግዲህ መሪነት ‹ሰው ተኮር› ከሆነ ሰው ተኮር የሆነ ሥራ ደግሞ በሰው መለወጥ ላይ ያነጣጠረ ‹ለውጥ ተኮር› መሆን አለበት:: ስለዚህ የክርስቲያናዊ መሪነት ከፍ ያለው ግብ የሰው ሕይወት መለወጥ መሆን አለበት::

መለወጥ የአእምሮ፣ የአስተሳሰብ፣ የአመለካከት ለውጥን የሚያመለክት ሂደት ነው:: መለወጥ ከአንድ አቅጣጫ ወደ ሌላ መዞር ነው:: መለወጥ ከከፉ መንገድ መመለስና በጽድቅ መንገድ መሄድ ነው:: ከመለወጥ በፊት የኃጢአት መደምሰስ ይቀድማል (ሐዋ 3:19):: መለወጥ ከቀደመው የኃጢአት ኑሮ ንስሐ በመግባት ወደ እግዚአብሔር ዘወር ማለት ነው (ሐዋ 26:20):: ይህ የደቀ መዝሙርነት ሕይወት ለእድሜ ዘመን ሁሉ በመታደስ የሚቀጥልና የክርስቶስን ክብር በማንጸባረቅ የሚያድግ ነው (2ቆሮ 3:18):: ይህ ነው የጽድቅ ጎዳና::

ሰው ወደ ጌታ የሚቀርበውና ክርስቲያን እንዲባል የሚያስችለው ወንጌል ነው:: በማንኛውም የመሪነት ተግባር ላይ ለተሰማራ ክርስቲያናዊ መሪ ክርስቲያን ተብሎ እንዲጠራ ያደረገው ወንጌል ነው:: ወንጌል የሕይወት በር ስለሆነ ክርስቲያን ሁሉ ወንጌልን እንዲወድ ይጠበቃል::

ስለሆነም በወንጌል አማካይነት ዳግመኛ ከመንፈስ ቅዱስ በመወለድ አዲስ ፍጥረት የሆነ ሰው ሁሉ ወንጌልን ይወዳል፤ ስለ ወንጌል ይመሰክራል፤ ይዘምራል፤ ለሌላውም ይናገራል:: በሕይወቱ ቀዝቃዜ ከሌለበት በስተቀር ወንጌል ሁልጊዜ ትኩስ የዕለት የምሥራች ዜናው ነው:: ትናንት ዳግመኛ ስለ መወለዱ፤ ዛሬ ስላለው ሰላምና እረፍት፤ ነገ ስለሚጠብቀው ተስፋ ይናገራል::

ስለዚህ የክርስቲያን መሪ ማንነት መገለጫው በወንጌል ነው፤ የሚኖረውም ለወንጌል ነው:: ወንጌልን ለመስማትና ለማስማት አይታክትም:: ራሱ ‹ወንጌል ሰባኪ› ተብሎ ባይጠራም ወንጌል እንዲሰበክና ሰዎች ሁሉ የክርስቶስን አዳኝነት ሰምተው ከእግዚአብሔር ጋር እንዲታረቁ ይጸልያል፤ ባለው ይደግፋል፤ የሚቻለውን ሁሉ ያደርጋል:: ይህ ለክርስቲያን መሪ በተሰማራባት ስፍራ በቤተ ክርስቲያን ወይም ድርጅት ከተሰጠው የሥራ ዝርዝር ሁሉ በላይ ከፍ ያለ የሕይወቱ የሁልጊዜ ተልዕኮ ነው:: በተሰማራበት መስክ ሁሉ የተሰጠውን የመሪነት የሥራ ዝርዝር እያከናወነ ሁልጊዜ ከሁሉ በላቀውና ዘላለማዊ ውጤት ባለው የሰው ሕይወት መለወጥ ላይ ማነጣጠር አለበት::

ስለሆነም የመሪነት ሕንጻ በር ስለሆነው ወንጌል ምንነትና አፈጻጸሙ አጠር አድርገን እንመልከት::





## 4.1 ወንጌል የሚሰበከው ለፍጥረት ሁሉ ነው::

ወንጌልን በመስበክ ሰዎችን ደቀ መዛሙርት የማድረግ ተልዕኮ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከትንሣኤው በኋላ ለደቀ መዛሙርቱ የሰጣቸው ትዕዛዝ ነው:: እንዲህ ሲል:- «ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ:: እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸዉ:: እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ» (ማቴ 28:18-20):: ይህ ትዕዛዝ ‹ታላቁ ተልዕኮ› በመባልም ይታወቃል::

በሌላም ስፍራ ጌታ ደቀ መዛሙርቱን «ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ። ያመነ የተጠመቀም ይድናል፤ ያላመነ ግን ይፈረድበታል» (ማር 16:15-16) አላቸው:: እንዲሁም ወደ አባቱ ቀኝ ከማረጉ በፊት «ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፣ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ በምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ» (ሐዋ1:8) በማለት ደቀ መዛሙርቱን አዟቸዋል::

ወንጌል መስበክ የክርስቶስን አዳኝነት ላልሰማ ሰው ሁሉ አዳኝነቱን ማብሰር ነው:: የወንጌል መሠረታዊ መልዕክቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ለዓለም ኃጢአት በመስቀል ላይ መከራን ተቀበለ፣ ሞተ፤ በሦስተኛውም ቀን ተነሣ፣ በእርሱ የሚያምኑ ሁሉ የዘላለም ሕይወት ይወርሳሉ የሚል ነው:: ይህ የምሥራች ቃል (መልካም ዜና) ነው::

የክርስቶስ መስቀል የመታረቂያ ሥፍራ ነው:: እግዚአብሔርና ሰው የታረቁበት፣ ሰውና ሰውም የታረቁበት ነው:: «በእርሱም በኩል በመስቀሉ ደም ሰላም አድርጎ በምድር ወይም በሰማያት ያሉትን ሁሉ ለራሱ እንዲያስታርቅ ፈቃዶአልና» (ቆላ 1:20) እንደሚል

በመስቀል ላይ የፈሰሰው የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ሰላምን ያመጣ ለሰላም የፈሰሰ ደም ነው:: እንዲሁም «እርሱ ሰላማችን ነውና፣ ሁለቱን ያዋሐደ በአዋጅ የተነገሩትንም የትእዛዛትን ሕግ ሽሮ በመካከል ያለውን የጥል ግድግዳን በሥጋው ያፈረሰ፣ ይህም ከሁለታቸው አንድን አዲስን ሰው በራሱ ይፈጥር ዘንድ ሰላምንም ያደርግ ዘንድ፣ ጥልንም በመስቀሉ ገድሎ በእርሱ ሁለታቸውን በአንድ አካል ከእግዚአብሔር ጋር ያስታርቅ ዘንድ ነው» (ኤፌ 2:14-16)::

መስቀል:- ሰው ከዕዳ ነፃ የሚሆንበት ስፍራ ነው:: ሰው ሁሉ በኃጢአቱ ምክንያት ለእግዚአብሔር ባለ ዕዳ ሲሆን ይህ ዕዳ የተከፈለው በኢየሱስ ክርስቶስ የመስቀል ሞት ነው:: «በእንጨት የሚሰቀል ሁሉ የተረገመ ነው ተብሎ ተጽፎአልና ክርስቶስ ስለ እኛ እርግማን ሆኖ ከሕግ እርግማን ዋጀን» (ገላ 3:13) እንደሚል:: በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምን ሁሉ እርግማን የተወገደለት የኃጢአት ዕዳው የተከፈለለትና በምትኩ ነፃነትን ያገኘ ሰው ነው:: ይህ ነው አርነት፤ ይህም ነው እውነተኛ ለውጥ (ትራንስፎርሜሽን)::

እንግዲህ በየትኛውም የዓለም ክፍልና በማንኛውም ዘመን የሚኖር ክርስቲያን መሪ ሰው ሁሉ ይህን እርቅ እንዲያገኝና አርነት እንዲወጣ፤ ከጨለማ ወደ ብርሃን እንዲሻገር፤ የዘላለም ሕይወት በመቀበል ለዘላለም እንዲለወጥ ግብ አድርጎ የሚሠራ መሆን አለበት:: ይህ ነው ታላቅ መሪነት፤ ይህ ነው የእግዚአብሔርን ሀሳብ ማገልገል:: ከዚህ የበለጠ ተግባር የለም::

## 4.2 የመንግሥት ወንጌል

ክርስቲያናዊ መሪ እንደማንኛውም ዳግመኛ የተወለደ ክርስቲያን ምድራዊና ሰማያዊ ዜግነቶች አሉት:: እነዚህ ሁለት ዜግነቶች





የየራሳቸው የሆነ ባሕርያት አላቸው:: ክርስቲያን መሪ በምድር እየኖረና ‹ምድራዊ› የሚባል ተግባር እያከናወነ እይታውና ድርጊቱ የሚገዛው ግን በሰማያዊ እሴቶች ነው:: የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጋ እንደመሆኑ በዚህ መንግሥት ሥርዓት መሠረት መኖር ይጠበቅበታል::

ወንጌል ኢየሱስ ክርስቶስ የሰበከው የመንግሥት ወንጌል ነው (ማቴ 9:35፤ 24:14፤ ማር 1:14፤ ሉቃ 8:1):: የመንግሥት ወንጌል - ንጉሥ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ አስቀድሞ በነቢያት እንደተነገረው መምጣቱንና በእጁ ታምራት መደረጉን ((ኢሳ 35:4-6፤ ማቴ 11:2-6) የሚያውጅ የምሥራች ቃል ነው::

የመንግሥት ወንጌል የሚናገረው የእግዚአብሔር ፍጹም ገዢነት ስለሰፈነበትና በኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ የጠላት መሸነፍ ስለተረጋገጠበት መንግሥት ነው:: የእግዚአብሔር መንግሥት በሙላት ወደፊት የሚጠበቅ ሆኖ ሳለ የእግዚአብሔር ገዢነት አሁንም በመካከላችን አለ (ማቴ 12:28):: የእግዚአብሔር መንግሥት የመብልና መጠጥ ነገር አይደለም (ሮሜ 14:17):: የእግዚአብሔር መንግሥት በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአታቸው የታጠቡ ሕዝብ (ራእ 1:6፤ 5:10) የሚኖሩባት ዘላለማዊ መንግሥት ናት::

የመንግሥቱ ዜጋ ለመሆን መስፈርቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ነው:: የመንግሥቱ ዜጐች በምድር ዙሪያ የሚገኙ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም የተዋጁ ሰዎች ሁሉ ናቸው:: ስለዚህ ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የዚህ መንግሥት ዜጋ መሆን አይችልም:: ከኃጢአታቸው የሚመለሱ ሁሉ ቀራጮችና አመንዝሮችም ይገቡባታል (ማቴ 23:31):: የኃጢአትን ሥርየት ያገኙ ሁሉ ከጨለማው ሥልጣን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ይፈልሳሉ (ቆላ 1:13)::

ይህ ከዲያብሎስ ግዛት ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መፍለስ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የሚገኝ ለሰው ሁሉ የተሰጠ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው:: ይህን ታላቅ የምሥራች ማስታወቅ የክርስቲያን መሪ የዘወትር ተልዕኮ ነው:: መሪ ራሱ የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጋ መሆኑን በማወቅ የመንግሥቱን እሴቶች በቃልና በተግባር እያሳየ እንዲኖር ይጠበቅበታል:: በዚህ ድርጊቱ የወንጌል አገልጋይ ነው::

## 4.3 የክርስቶስን ፍቅር የሚገልጽ መልካም ሥራ

ቤተ ክርስቲያን ወደ «ውጭ» ከሚኖሯት ሁለት ትልልቅ ተግባሮች መካከል የምሥራቹን ቃል መስበክ ሲሆን ሌላው መልካም ሥራ ማከናወን ነው:: በመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም መሠረት መልካም ሥራ በኢየሱስ ክርስቶስ ከማመን የሚመነጭ ለሰዎች የሚደረግ በጎ ተግባር ወይም አገልግሎት ነው:: ይህም የተራቡትን በማብላት፣ የተጠሙትን በማጠጣት፣ የታረዙትን በማልበስ፣ የታመሙትን በመንከባከብ፣ የታሰሩትን በመጠየቅ፣ ችግረኞችንና ድሆችን በመርዳት፣ ለመበለቶችና ወላጆች ለሌላቸው ልጆች በመጠንቀቅና በመሚገት የሚገለጽ እግዚአብሔርን የሚያከብር ሥራ ነው:: ይህ «የምሕረት» አገልግሎት ነው (ሉቃ 10:37)::

ለእግዚአብሔር ክብር የሚደረግ የፍቅር ርኅራኄ የዘር፣ የቋንቋ ልዩነት፣ የሀገር ድንበር አይገድበውም:: ወንጌል የሚሰበከው ለሁሉም ሰው የመሆኑን ያህል መልካም ሥራም የሚደረገው በእግዚአብሔር አምሳል ለተፈጠረ፣ ለተቸገረ ለማንኛውም ሰው ነው:: ስለዚህ «ባልንጀራዬ ማን ነው?» (ሉቃ 10:29) ለሚለው ጥያቄ መልሱ የተቸገረና እርዳታ የሚያስፈልገው ሰው ሁሉ ነው:: የጌታ ቃል እንደሚል ለሚወዱን ብቻ መልካም ብናደርግ በእግዚአብሔር ፊት ሞገስ የለውም::





ባልንጀራ «ምሕረትን» የሚፈልግ በችግር ላይ የወደቀ ሰው ነው፡፡ «ምሕረት» የሚያስፈልገው ሰው መጠላላት ካለበት ከሌላኛው ወገን እንኳን ቢሆን ክርስቲያን መሪ ግን እነዚህን ግድግዳዎች ሁሉ አልፎ የሚሄድና በእግዚአብሔር ስም ለሌላው መልካም የሚያደርግ ነው:: ጌታ በሉቃ 10:29-37 እንዳስተማረው:- በወንበዴዎች እጅ ለወደቀው ሰው ባልንጀራ የሆነው ካህኑ ወይም ሌዋዊው ወይም አይሁዳዊው ሰው ሳይሆኑ፣ የራራለትና ከወደቀበት ያነሣው፣ በቁስሉ ላይ ዘይትና የወይን ጠጅ አፍስሶ ያሰረለት፣ ከገንዘቡም አውጥቶ የከፈለለት ሰው ነው:: ለድሀ የሚራራ እግዚአብሔርን ያከብራል (ምሳ 14:31)::

«ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ» (ማቴ 22:39፤ ማር 12:31) የሚለው ታላቁ ትእዛዝ በመባል ይታወቃል:: ታላቁ ትእዛዝ እግዚአብሔር ለሰው ያለውን ፍቅርና ርኅራኄ የመግለጫ መንገድ ነው:: በክርስቶስ ስም የተደረገ መልካም ሥራ እግዚአብሔርን የሚያከብር የርኅራኄ ተግባር ነው:: በክርስቶስ ስም ያልተሰጠ ውኃ ግን የሰው ችሮታ ብቻ ነው::

የታላቁ ትእዛዝ መግለጫ የሆነው ባልንጀራን እንደ ራስ መውደድ የእግዚአብሔር ፍቅር መግለጫ ስለሆነ ራሱ ወንጌል ነው:: ታላቁ ተልእኮ ወንጌልን በቃል በመስበክ ሰዎችን የጌታ ደቀ መዛሙርት ማድረግ ሲሆን ታላቁ ትእዛዝ ደግሞ በክርስቶስ ስም በሚደረግ መልካም ሥራ ወንጌልን መግለጽ ነው:: ወንጌልን ማስተማርም ሆነ በጌታ ስም የተራቡትን መመገብ ሁሉም እግዚአብሔር ለሰው ያለውን ፍቅርና ርኅራኄ ይገልጻሉ::

እንግዲህ ቀደም ሲል እንደተመለከትነው ክርስቲያናዊ መሪ ከተሰጠው ሥራ በላይ አንድ ትልቅ ተልዕኮ አንግቦ የሚሄድ ሰው ነው:: ይህ ተልዕኮ ባለበት ስፍራ ከተሰጠው የስራ ድርሻ በተጨማሪ ወደ ዓለም የተላከ የክርስቶስ መልእክተኛ መሆን ነው::

የክርስቶስን ወንጌል የሚናገር፤ የክርስቶስን ፍቅር የሚገልጽና ሰዎች ወደ ክርስቶስ እንዲቀርቡ አቅጣጫ የሚያሳይ ‹የሰማይ› ልዑክ ነው።


በአጠቃላይ <u>መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሪነት ‹ወንጌል ተኮር›</u> ነው። ትልቁ ግብ ወንጌል ነው፤ ዓላማው ወንጌል ነው። ታላቁን ተልዕኮና ታላቁን ትእዛዝ መፈጸም በሁሉም ክርስቲናዊ መሪ የሥራ ዝርዝር ውስጥ (በግልጽም ሆነ በተዘዋዋሪ) መታጣት የሌለበት የሥራ ኃላፊነት ነው። የቤተ ክርስቲያንም ሆነ የመንፈሳዊ ድርጅት መሪ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የሚሠራው ከእነዚህ ተልዕኮዎች ጋር የተያያዘ መሆን አለበት።

በመጨረሻም:- ለገነባነው ሕንጻ ጉልላት እናብጅለት። በምድር የሚደረገው አገልግሎት ሁሉ ማጠቃለያው ወደ ሰማይ መድረሱ በመሆኑ በሚቀጥለው ምዕራፍ ሁሉን ለእግዚአብሔር ክብር ስለማድረግ እንመለከታለን።





# ክፍል አምስት:-
# የክርስቲያናዊ መሪነት ሕንጻ ጉልላት:-
# ሁሉን ለእግዚአብሔር ክብር ማድረግ




ክርስቲያናዊ ሕይወት ሁሉን ለእግዚአብሔር ክብር የማድረግ አንድ ዋና ዓላማ አለው። ሁሉም ተግባር ከዚህ ዓላማ አንጻር ይመዘናል። በእንቅስቃሴውና እርምጃው ሁሉ «ይህ እግዚአብሔርን ያከብራልን?» በማለት ይጠይቃል። ይህን ሚዛን የማይደፋ ተግባር ሁሉ በቀላሉ ይጣላል። ክርስቲያን

እግዚአብሔርን የሚያከብሩ ተግባሮችን በጽድቅ መንገድ ለእርሱ ክብር ይሠራል:: መጽሐፍ ቅዱሳዊው ክርስትና እንዲህ ነው::

የክርስቲያናዊ መሪነት ዋናው ቁም ነገር ሥራን ከማከናወን፣ ብዙ ሰዎችን በአንድ ዓላማ ዙሪያ አስከትቶ «ድንቅ» የሚባል ፕሮጀክት መፈጸም አይደለም:: ክርስቲያናዊ መሪነት እግዚአብሔር ለዚያ ዘመን ያለውን ፈቃድ መረዳት፣ በእርሱ መሪነት ሥር መፈጸምና ክብርን ለእርሱ መስጠት ነው::

ሁሉን ለእግዚአብሔር ክብር በማድረግ እርሱን ማክበር የቤተ ክርስቲያን ዋና ዓላማ ነው:: እግዚአብሔር ክብርንና ግርማን የለበሰ እጅግ ታላቅ አምላክ ነው (መዝ 104:1):: ክብሩ[54] ታላቅ ነው (መዝ 138:5፣ 113:4)፣ በክብሩም ባለጠጋ ነው (ኤፌ 3:16):: የእግዚአብሔር ግርማ ያስፈራል፣ ያስደነግጣል (ኢዮ 37:22፣ ኢሳ 2:10):: እግዚአብሔር የክብር አምላክ ነው (ሐዋ 7:2)::

ስለሆነም እግዚአብሔር ክብር ሊሰጠው የሚገባ አምላክ ነው:: ክብር የእግዚአብሔር መግለጫ ነው:: መጽሐፍ «እግዚአብሔርን የምትፈሩ አመስግኑት፣ አክብሩት፣ ...ፍሩት» (መዝ 22:23)፣ «ለእግዚአብሔር ክብርን ስጡ» (ኢሳ 42:12)፣ «ክብርን ኃይልን ለእግዚአብሔር አምጡ ...በቅድስናው ስፍራ በፊቱ ስገዱ» (ዜና 16:28፣29) እንደሚል እግዚአብሔርን ማክበርና እርሱን ማመስገን የእርሱ የሆኑት እድል ፈንታቸው ነው::

[54] ከዚህ ቀጥሎ ያለው በአብዛኛው የተወሰደው በዚሁ ጸሐፊ ከተጻፈው «ቤተ ክርስቲያን» ከሚለው መጽሐፍ ነው:: ክብር የሚለው ቃል ካቦድ ከሚለዉ የዕብራይስጥ ቃል የተገኘ ሲሆን ትርጉሙም «ከብደት» ወይም የአንድ ነገር እሴት/ ከበሬታን (worth) ያመለክታል:: የእግዚአብሔር ክብር በአንድ ቦታ በመገኘቱ «የጌታም ክብር በዙሪያቸዉ አበራ» (ሉቃ 2:9) እንደሚለዉ ወይንም በሚያስደንቅ የእጁ ሥራዎች (መዝ 19:1) ሊገለጽ ይችላል:: ጌታ ኢየሱስ ወደ አብ ሲጸልይ «የሰጠኸኝን ክብር እኔ ሰጥቻቸዋለሁ» (ዮሐ 17:22) እንዳለዉ ክብር በመንፈሳዊ (ማለትም በማይታይ) ሁኔታ ሊገለጽ ይችላል:: (Hb: Kabowd (Kaw-bode) - Splender or copiousness; Gk: doxa (dox' ah) glory, honour). ክብር ከአንድ ቦታ ሲለቅ ደግሞ (Hb: Iy-Kabowd - inglorious, Ikabod) ይባላል::





ክርስቲያኖች እግዚአብሔርን የሚያከብሩት በአኗኗራቸው (በኑሯቸው) ሁሉ ነው:: እግዚአብሔር የሚከብረው ምስጋና ለእርሱ በማቅረብ (መዝ 50:15)፣ እርሱ የሰጠውን ተስፋ ሳይዝሉ በእምነት በመጠበቅ (ሮሜ 4:20)፣ ለእግዚአብሔር ብዙ ፍሬ በማፍራት (ዮሐ 15:8)፣ በጽድቅ ፍሬ በመሞላት (ፊሊ 1:11)፣ ስለ ክርስቶስ በመነቀፍ (1ጴጥ 4:14፣16)፣ ስለ እርሱም በመሞት (ዮሐ 21:19) ሁሉ ነው::

አገልጋይ ከእግዚአብሔር በተሰጠው ጸጋ እግዚአብሔርን በማክበርና በታማኝነት ሲያገለግል እንዲሁም የሚናገር እንደ እግዚአብሔር ቃል ሲናገር እግዚአብሔር ይከብራል (1ጴጥ 4:11):: እግዚአብሔር በባሪያዎቹ በኩል በሚያደርገው ድንቅና ታምራት ይከብራል (ሐዋ 19:11-17):: የበሽተኞች መፈወስ ለእግዚአብሔር ክብር ነው (ሐዋ 4:21)::

እግዚአብሔር በነገር ሁሉ ይከብር ዘንድ (1ጴጥ 4:11) ክርስቲያኖች በሥጋቸው እግዚአብሔርን እንዲያከብሩና (1ቆሮ 6:20) የሚያደርጉትን ሁሉ ለእርሱ ክብር እንዲያደርጉት (1ቆሮ 10:31) ተጠርተዋል:: በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የእግዚአብሔር ልጆች ለመሆን ዳግመኛ የተወለዱት የጸጋውን ክብር ያመስግኑ ዘንድ ነው (ኤፌ 1:6):: በአጠቃላይ ክርስቲያን በኑሮውና በአገልግሎቱ በመከራውና በሞቱ እግዚአብሔርን ያከብራል (ዮሐ 21:19፣ 1ጴጥ 2:21):: ለክርስቲያን እንዲሁም ለቤተ ክርስቲያን ሕይወትና አገልግሎት ሁሉ ለእግዚአብሔር ክብር ነው:: ይህም የተገኘው በክርስቶስ የመስቀል ሞት ነው (ዕብ 2:10)::

የእግዚአብሔር ክብር፡- የእርሱ ታላቅነት፣ በአንድ ቦታ በሙላት መገኘቱ፣ የእርሱ ሙላት አንድን ቦታ መሸፈን ነው (ዘጸ 16:10፣ ኢሳ 6:3)፡፡ እግዚአብሔር በሕዝቡ ደስ ሲለው መሥዋዕቱን ሲቀበል ክብሩን ለሕዝቡ ይገልጣል (ዘሌ 9:6፣22)፡፡ ከዚህም የተነሣ ታላቅ ደስታ፣ እልልታ፣ አምልኮ ይሆናል፡፡ የእግዚአብሔር ክብር በሚገለጥበት በዚያ ታላቅ ብርሃን ይሆናል (ኢሳ 60:1-2፣ ራእ 21:11፣23)፡፡ ለሰው ክብርን የሚሰጥ እግዚአብሔር ነው (መዝ 84:11፣ ዳን 2:37)፡፡

የሰማይ ሠራዊት ዘወትር በእግዚአብሔር ፊት እየሰገዱ ክብር ይሰጡታል (ራእ 4:11)፡፡ ምድር የእግዚአብሔርን ክብር በማወቅ ትሞላለች (ዕን 2:14)፣ በእግዚአብሔር ክብር ተሞልታለች (ኢሳ 6:3)፡፡

እግዚአብሔር ወደ ሰፈር ሲመጣ (ዘጸ 19:16) እርሱ መጥቷልና ክብሩ ሰፈሩን ይሞላል፡፡ የእግዚአብሔር ታቦት ሲማረክ ደግሞ «ኢካቦድ» ሆኗል (1ሳሙ 4:21)፡፡

የእግዚአብሔር ክብር መገለጥ ለእርሱ ከሚቀርበው አምልኮ ጋር ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት አለው፡፡ እግዚአብሔር በአንድነትና በመቀደስ ሆነው እርሱን በሚያመልኩት መካከል ክብሩን ይገልጻል፡፡ በአንድ ልብ በሆኑ ወንድሞች መካከል የእግዚአብሔር በረከት አለ፡፡ በመቀደስም እግዚአብሔርን ማየት አለ፡፡ ፍቅርና አንድነት የእግዚአሔርን ክብር ለማየት ቀዳሚ ናቸው፡፡ እግዚአብሔር በሕዝቡ መካከል በክብር እንዲገኝና ድንቅን እንዲያደርግ አስቀድሞ ሕዝቡ ይቀደስ ዘንድ ያስፈልጋል፡፡

እግዚአብሔር እርሱን በመፍራትና በመቀደስ በፊቱ በሚመላለሱትና በሚያመልኩት መካከል በክብር ይገለጻል፡፡ በመቀደስ በፊቱ በሚመላለሱና በአንድነት ሆነው በአንድ ቃል





ለእርሱ ክብር ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በሚዘምሩት መካከል በክብሩ ይመላለሳል፡፡ ሰሎሞን በሠራው ቤተ መቅደስ እንደሆነው፡-

በዚያም ካህናት ሁሉ ተቀድሰው ነበር ...መለከቱንም የሚነፉ መዘምራኑም በአንድነት ሆነው እግዚአብሔርን እያመሰገኑና እያከበሩ፡- እግዚአብሔር ቸር ነውና፣ ምሕረቱም ለዘላለም ነውና እግዚአብሔርን አመስግኑ እያሉ በአንድ ቃል ድምፃቸውን ወደ ላይ ከፍ አድርገው በመለከትና በጸናጽል በዜማም ዕቃ ሁሉ እግዚአብሔርን ባመሰገኑ ጊዜ፣ ደመናው የእግዚአብሔርን ቤት ሞላው፡፡ የእግዚአብሔርም ክብር የእግዚአብሔርን ቤት ሞልቶት ነበርና ካህናቱ ከደመናው የተነሣ መቆምና ማገልገል አልተቻላቸውም (2ዜና 5:11-14)፡፡

መዘምራኑ በአንድነት መቅረባቸው፣ መቀደሳቸው፣ በዜማ ዕቃ ሁሉ ማመስገናቸው ለጌታ እግዚአብሔር ደስ የሚያሰኝ አምልኮ ለማቅረብ ነው፡፡ እግዚአብሔር የሚቀርብለት አምልኮና አገልግሎት ደስ ሲለው ያን ጊዜ እግዚአብሔር ከበረ እንላለን፡፡ እርሱም በሚወደው መንገድ ክብሩን ይገልጻል፡፡ በዚህ ጊዜ የተገለጸው ክብር በእግዚአብሔር ቤት ቆሞ ማገልገል የማያስችል ደመና፣ ክብደት ያለው ደመና፣ የክብር ደመና፣ እግዚአብሔር ደስ መሰኘቱን የሚገልጽበት ክብር የሞላበት ደመና ነው፡፡ የአገልግሎት ከፍተኛው ደረጃ የእግዚአብሔር ክብር መገለጥ ነው፡፡ «ለአብ ከዘላለም እስከ ዘላለም ክብር ይሁን» (ገላ 1:5)፡፡

እግዚአብሔርን ማክበር የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ዓላማ ነበር፡፡ ጌታ ኢየሱስ ሊያደርገው የተሰጠውን ሥራ ፈጽሞ እግዚአብሔርን አከበሯል (ዮሐ 17:4)፡፡ ለእግዚአብሔር አብ ክብር በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ በኢየሱስ ስም ይንበረከካሉ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደሆነ ይመሰክራሉ (ፊል 2:10-11)፡፡

አማኞችም ለክርስቶስ ክብር ምስጋና ይሆናሉ (ኤፌ 1፡12-14)። «ለእርሱ በቤተ ክርስቲያን ክብር ይሁን» (ኤፌ 3፡21)። «ለእርሱ አሁንም እስከ ዘላለም ቀን ድረስ ክብር ይሁን፤ አሜን» (2ጴጥ 3፡18)።

## ውድ አንባቢ ሆይ፡-

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እምነት ሲያስተምር «እንግዲህ እነዚህን የሚያህሉ ምስክሮች እንደ ደመና በዙሪያችን ካሉልን» ይልና «በፊታችን ያለውን ሩጫ በትዕግሥት እንሩጥ» (ዕብ 12፡1-2) ይላል። በዚህ ዘመን ያለን ክርስቲያኖች ስለ እምነት «አዲስ» ነገር አናመጣም። የሚጠበቅብን ያሉልንን ምስክሮች ምሳሌነት መከተል ነው። ከምሳሌዎቹ ሁሉ የላቀው ምሳሌ ዛሬ «በእግዚአብሔር ዙፋን ቀኝ» የተቀመጠው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

ለመንፈሳዊ መሪነትም እንዲሁ ነው። ዛሬ ለክርስቲያናዊ መሪነት የሚሆኑ ምስክሮች እንደ ደመና በዙሪያችንን አሉልን። ቀደም ሲል በዚህ መጽሐፍ ቅጽ ፫ የተመለከትነው ይህንኑ ነበር። የእኛ ድርሻ ክርስቲያናዊ መሪነትን እንደገና ለመተርጎም መሞከር ሳይሆን «ኢየሱስን ተመልክተን በፊታችን ያለውን ሩጫ በትዕግሥት» መሮጥ ነው።

ሐዋርያው ጳውሎስ «ደግሜ እላለሁ» (ፊል 4፡4)፤ የዕብራውያንም ጸሐፊ «ከተናገርነው ዋና ነገሩ ይህ ነው» (ዕብ 8፡1) ሲል(ሉ) የሚጽፍበትን ዓላማ በማጠቃለልና በአጽንኦት መናገሩ እንደነበረ ይታወቃል። በመልካም እረኝነትም ዋና ነገሩ እግዚአብሔር የሕዝቡ መሪና እረኛ መሆኑን በማወቅ የእርሱን ሀሳብ ማገልገል ነው። የአንድ መሪ መንፈሳዊነቱ የሚገለጸው የክርስቶስ አካል የሆነችው ቤተ ክርስቲያን «አንድ አካል» መሆኗን በመገንዘብና የመንፈስን አንድነት በመጠበቅ በፍቅር ስመራ፤ ከተለሰከው ሁሉ





ትልቁ ተልዕኮ ወንጌል እንዲስፋፋ ማገዝ መሆኑን ሲገነዘብ፤ የእግዚአብሔርም ቤት የጸሎትና የሰላም ቤት እንዲሆን ሲተጋ፤ ራሱም በመልካም ባሕርይ እየኖረ አገልግሎቱን ለእግዚአብሔር ስም ክብር ሲያደርግ ነው።

ይህ ሲሆን «...መሪዎች ስለ መሩ፤ ሕዝቡም ነፍሳቸውን በፈቃዳቸው ስለ ሰጡ፤ እግዚአብሔርን አመስግኑ» (መሳ 4፡2) እንላለን። ይህ ሲሆን ‹ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ዘረጋች፤ እግዚአብሔርም እጇን ዘርግቶ ያዛት፤ ታደጋት፤ ፈወሳት፤ በምድርም ለመደነቂያና ብርሃን አደረጋት› እንላለን። ይህን የሚጠባበቅ ሁሉ ከዚህ ጸሐፊ ጋር አሜን ይበል። አሜን።

# ዋቢ መጻሕፍት Bibliography

## Bibles

መጽሐፍ ቅዱስ በ1879 ዓ.ም. ከታተመው እንደገና የታተመ፤ የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር

መጽሐፍ ቅዱስ (1962 ዓ.ም)፤ በኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር

መጽሐፍ ቅዱስ ቀለል ባለ አማርኛ የተተረጎመ (1980 ዓ.ም)፤ በኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር

መጽሐፍ ቅዱስ አዲሱ መደበኛ ትርጉም (1993 ዓ.ም)፤ በኢንተርናሽናል ባይብል ሶሳይቲ

The American Standard Version of 1901 (ASV).

Contemporary English Version, 1995, (CEV)

English Standard Version (ESV)

God's Word to the Nations Bible Society (GN).

Good News Bible, 1992, Second Edition, (GNB)

International Standard Version, 1992 (ISV)

King James Version of the Holy Bible (KJV).

Modern King James Version, MKJV).

New International Version (NIV)

Revised Standard Version of The Holy Bible (RSV)

The Leadership Bible

The Maxwell Leadership Bible, 2002, Thomas Nelson Bibles





## *Bible Commentaries and Concordances*

Adam Clarke's Commentary on the Bible (Clarke)

Albert Barnes Notes on the Bible (Barnes)

Critical and Explanatory Notes on the Whole Bible

John Gill's Exposition of the Entire Bible (JG)

John Wesley's explanatory Notes on the Whole Bible

Mathew Henry's concise commentary on the Whole Bible.

Robert Jamieson, A.R. Fausset and David Brown (JFB) Commentary

Strongs Exhaustive Concordance of the Bible

The Living Word Commentary series

Thomas Robertson, Word pictures in the New Testament,

Treasury of Scriptural Knowledge, Canne, Browne, Blayney, Scott and others.

Vincent's Commentary on the Greek New Testament.

Wycliffe Commentary

## Bible Dictionaries

Fausset's Bible Dictionary

M.G. Easton, Illustrated Bible Dictionary, Third Edition, published by Thomas Nelson, 1897.

International Standard Bible Encyclopedia, 1939, Wm. B.

International Standard Bible Encyclopedia, 1939, Wm. B. Eerdmans Publishing Company

King James Dictionary

Nelson's Bible Dictionary

Strong, James. Strong's Hebrews and Greek Dictionaries

The New Dictionary of Theology (ed.) (1994) Inter Varsity Press,

Thompson's Chain Topics

R. A. Torrey's New Topical Textbook.

Unger's Bible Dictionary

Vine's Expository Dictionary

# Books

መልሳቸው መስፍን (1998 ዓ.ም) አደራ፡- ወጣቱ ጢሞቴዎስ አደራ ጠባቂ፤ አንድነት ማተሚያ ድርጅት፤ አ.አ.

__________ (1998 ዓ.ም) «ጨለማም አላሸነፈውም»፡- የዮሐንስ ወንጌል ማብራሪያ፤ አንድነት ማተሚያ ድርጅት፤ አ.አ.

__________ (1997 ዓ.ም) ቤተ ክርስቲያን፡ «እርሷም አካሉና ሁሉን በሁሉ የሚሞላ የእርሱ ሙላቱ ናት»፤ ርኆቦት ማተሚያ ድርጅት፤ አ.አ.

Banks, Robert and Bernice m. Ledbetter (2004) Reviewing Leadership: A Christian Evaluation of Current Approaches, Baker Academic, Grand Rapids, Michigan.

Bass, Bernard M. (1985). "From transactional to transformational leadership: Learning to share the vision." *Organizational dynamics*, Vol. 18, 3: 19-31.

Baughen, Michael (1978) The Moses Principle: Leadership and the venture of Faith, Harold Shaw Publishers, Wheaton, Illinois

Berry, Joyce K. and John C. Gordon, Editors, (1993) Environmental Leadership: Developing Effective Skills and Styles, Island Press.



መልካም እረኝነት ቅጽ ፩

Blackaby, Henry and Richard (2001) Spiritual Leadership: Moving People to God's Agenda, C.O.S. Publishers, Singapore.

Boa, Kenneth (2006) The Perfect Leader: Practicing The Leadership Traits of God, Cooks Communication Ministries, Colorado Springs, Colorado.

Burns, James McGregor (1978). *Leadership*. New York: Harper and Row.

Clinton, Robert J. (1988), the Making of a Leader, Navpress, Colorado Springs, Colorado.

D'Souza, Anthony ((1994) Developing The Leader Within You: Strategies for Effective Leadership, OM Books, Secunderabad

__________ (2006) Empowering Leadership: Lead with Vision and Strategy, Haggai Institute

__________ (2006) Empowered Leadership: Your Personal Guide to Self Empowerment, Haggai Institute.

Dever, Mark (2004) Nine Marks of a Healthy Church, Cross Way Books, Wheaton, Ill.

Engstrom, Ted W. Ten qualities of the Best Non-Profit Christian Leaders (mimeographed) CEO Dialogues, Inc. 3/93

Ford, Leighton (1991) Jesus: The Transforming Leaders, Hodder and Stoughton, London.

George, Carl F. and Robert E. Logan (1996) Leading and Managing Your Church, Fleming H. Revell, Grand Rapids.

Gordon, Bob (1990) The Leader s Vision, Sovereign World, Tonbridge, Kent.

Greenleaf, Robert K. (1991) Servant Leadership: A journey into the nature of Legitimate Power and Greatness by Ibid.

Haggai, John Edmund (2006) Lead on: Leadership That Endures in a Changing World, Haggai Institute

_____________ (1989) Be careful what you call impossible, Harvest House publishers, Eugene, Oregon.

Hocking, David L. (1979) Be A Leader People Follow, Regal Books, Glendale, California.

House, Robert and Phillip Podsakoff (1994), Outstanding leadership theory.

Houston, Tom (1987) King David: Lessons on leadership from the life of David, MARC Europe.

Julian, Larry (2002) God is My CEO: Following God's principles in A Bottom-line World, Adams Media Corporation, Avon, Massachusetts.

Macchia, Stephn A. (1999), Becoming a Healthy Church: Ten Traits of a Vital Ministry, Baker Books, Grand Rapids.

Mason, John (1990) An Enemy Called Average: why settle for less than your best? Kingsway Publications, Eastbourne,

Maswanganyi, Elijah and Kevin J. Conner (2000) *Biblical Principles of Leadership: Two are better than one*, second edition, Hebron Press, Tzaneen, SA.

McLean, J.W. and William Weitzel in their book, Leadership: Magic, Myth or Method, define leadership as

Merriam Webster's 11th Collegiate Dictionary.

Moore, Beth (2001) To Live is Christ: Embracing the passion of Paul, Monarch Books, Mill Hill, London.





Myra, Harold and Marshall Shelley (2005) The Leadership Secrets of Billy Graham, Zondervan, Grand Rapids.

Osei-Mensah, Gottfried, (1990) *Wanted: Servant Leaders*, Africa Christian Press.

Roberts, Randal (Ed) (1999) Lessons in Leadership: Fifty Respected Evangelical Leaders Share Their Wisdom on Ministry, Kregel publications, Grand Rapids, MI.

Rush, Myron (2004) Management: A Biblical Approach, Cooks Communication Ministries, Colorado Springs, Colorado.

Sanders, J. Oswald (1967), Spiritual leadership, Marshall Morgan and Scott Publications Ltd.

Stott, John (2002), Basic Christian Leadership: Biblical Models of Church, Gospel and Ministry, Inter Varsity Press

Tekeste Teclu (1995) A Participative Leadership: A Study of Faculty and Administrators in a Lutheran Liberal Arts College, A dissertation submitted in partial Fulfillment of the Requirements of the Degree of Doctor of Education, University of Northern Iowa.

_______ (1992) Participation and organizational Effectiveness Reflected in local churches, in Partial fulfillment of the requirements of of the degree of Master of Arts in Leadership, Augsburg college, Minneapolis.

Thrall, Bill; Bruce McNicol, Ken McElrath, (1999) The Ascent of a Leaders, Leadership Catalyst, Inc.

UN, Press Release SG/SM/7808.

Youssef, Michael (1986) The Leadership style of Jesus: How to Develop the Leadership qualities of the Good Shepherd, Victor books, SP Publications, Wheaton

## Electronically retrieved.

Blackaby, Richard (2001) Spiritual Leadership Broadman & Holman.

Christianity Today International/ Leadership Journal. September 9, 2003

Faulkner, Brooks; 7 Biblical Models of Leadership

Gangel, Kenneth O.; New Testament Principles of Leadership

Hybels, Bill; Finding Your Leadership Style: Ten different ways to lead God's people.

Karlgaard, Rich; Ideas: Peter Drucker On Leadership

Keathley, J. Hampton. The Distinctives of Christian Maturity and Leadership

Macchia, Stephen A.; Leadership Defined: Putting the pieces together.

Miller, Henry; Characteristics of Christian Leadership ©2005 Youth TRAIN

Smith, Fred; Spotting New Leaders (Part I and II) 8: signs of leadership potential.

www.brighthub.com/

www.mentorlink.org.

www.practicalmanagement.com

www.renewaljournal.com, Renewal Journal #15: Wineskins (2000:1)

ክርስቲያናዊ መሪነት የሚጀምረው የእግዚአብሔርን መሪነትና እረኝነት በመገንዘብ ነው፡፡ ሕንጻ ያለ ጽኑ መሠረት እንደማይገነባ ሁሉ እግዚአብሔር የሕዝቡ ሕያው መሪና እረኛ መሆኑን በእርግጠኛነት ሳያምኑ ክርስቲያናዊ መሪነት አይታሰብም፡፡

እግዚአብሔር ለእርሱና ከእርሱ ጋር የሚሠሩ ሰዎችን ለመሪነት ይመርጣል፡፡ የእነዚህ መሪዎች ክርስቲያናዊ ባሕርያትና ችሎታዎች በሕንጻ መሠረት ላይ እንደሚቆሙ ዓምዶች የሕንጻው ዋና ምሰሶዎች ናቸው፡፡

በሕንጻው ግንባታ የመሪነት ሕንጻ ድምድማቱ ፍቅር ነው፡፡ ጌታ ኢየሱስ ሲያስተምር «መልካም እረኛ እኔ ነኝ፡፡ መልካም እረኛ ነፍሱን ስለ በጎቹ ያኖራል» አለ፡፡ መልካም እረኛ በጎቹን የሚወድና በበጎቹም የታወቀ ነው፡፡ ክርስቲያናዊ መሪም የክርስቶስ ፍቅር የገባው፤ የአገልግሎት አንቀሳቃሽ ሞተሩ የክርስቶስ ፍቅር የሆነና በወንድማማች መዋደድ በመኖር የመንፈስን አንድነት የሚጠብቅ ሰው ነው፡፡

ክርስቲያናዊ መሪነት በሰው ሕይወት መለወጥ (ትራንስፎርሜሽን) ላይ ያተኮረ ተግባር ሲሆን በምድር ላይ ከምንም ነገር በላይ የሰውን ሕይወት መለወጥ የሚችለው መለኮታዊ ኃይል የሆነው ወንጌል ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሪነት ለውጥ ተኮር ስለሆነ ወንጌል ተኮር ነው፡፡ ወንጌል ዘላለማዊ ውጤት ያለው የለውጥ በር ነው፡፡

የክርስቲያናዊ መሪነት ዋና ግብ የሆነው እግዚአብሔርን ማክበር የሕንጻው ጉልላት፤ ሰው የተፈጠረበት ምክንያት፤ የአገልግሎት ግብና ማጠቃለያ፤ የመኖር ትርጉም፤ የክርስቲያን ሁሉ የዘላለም ተግባር ነው፡፡

Designed & Printed @ Andnet Printers

ዋጋ 30 ብር